# <u>አሥረኛ ፡ የዲኑ ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫ ፡</u>

## ፲፱፻፷፩ ዓ. ም.

ክሊፍ ፡ ቶምሰን ፡ ፕሮፌሰርና ፡ ዲን ፤

የቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርስቲ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፤

## <u>በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ.ም. ፡ የተፈጸሙ ፡ ታላላቅ ፡ ክንውኖች ።</u>

ይህ ፡ በዲንነት ፡ የምሰጠው ፡ አራተኛውና ፡ የመጨረሻ ፡ መግለጫ ፡ ነው ።

ይህ ፡ መግለጫ ፡ የመጨረሻ ፡ በመሆኑ ፡ በሕሊናዬ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የተለያዩ ፡ ስሜቶች ፡ አድረውብኛል ። ግን ፡ ከሁሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እድገት ፡ በጣም ፡ አሰፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ የትምህርትና ፡ (የአካዳሚ) ፡ ምርምር ፡ ይዞታ ፡ ከፍ ፡ ባለ፡ ደረጃ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ለረዱት ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼ ፡ የማቀርበውን ፡ ከልቤ ፡ ከመነጨ ፡ ምሥጋና ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ የሚሰጠኝ ፡ ነገር ፡ የለም ። ቢሆንም ፡ ለወደፊቱ ፡ ብቁ ፡ የሆኑ ፡ እያሌ ፡ የሕዝብ ፡ አገልጋዮች ፡ ለማፍራት ፡ በፕሮግራማችን ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ መሻሻል ፡ መደረግ ፡ እንዳለበት ፡ ይገባኛል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ይህን ፡ መግለጫዬን ፡ የመጨረሻ ፡ የሚያደርገው ፡ የለም ። ላገር ፡ ዕድገት ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆኑት ፡ ነገሮች ፡ የሕግን ፡ ት/ቤት ፡ ተጠያቂ ፡ የማድረጉ ፡ ተግባር ፡ ለወደፊትም ፡ ይቀጥላል ። የሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈው ፡ እንደሚበልጥ ፡ እምነቴ ፡ ነው ።

## <u>የፋክልቲውን ፡ ሥራ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ የማስተላለፉ ፡ ጉዳይ ።</u>

የሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈው ፡ ይበልጣል ፡ ያልኩበት ፡ አንዱ ፡ ምክንያት ፡ ፋክልቲው ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ የመተላለፉ ፡ ጉዳይ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ በመፈጸሙ ፡ ነው ። ከአሥር ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ አልነበረም ፡ በዩኒቨርስቲ ፡ ደረጃ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የነበራቸው ፡ ሰዎች ፡ ካሥር ፡ ያነሱ ፡ ነበሩ ። ባለፉት ፡ አራት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የፋክልቲው ፡ አስተማሪዎች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሆኑበት ፡ ለውጥ ፡ አላንዳች ፡ መሰናክል ፡ ተከናውኗል ። እንዲሁም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ረዳት፡ ዲኑና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ዋና ፡ አዘጋጁ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሆነዋል ። እነኚሁ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስተማሪዎችና ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። በተጨማሪም ፡ እነኚሁ ፡ አስተማሪዎች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በመሆናቸው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ችግሮች ፡ ለመመርመር ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ አስተማሪዎች ፡ የበለጠ ፡ ችሎታ ፡ አላቸው ። ለሦስት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተገቢ ፡ የሥራ ፡ እድገት ፡ ለማግኘት ፡ በመርዳት ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ እየተሻሻለ ፡ ይሄዳል ፡ ብዬ ፡ በእርግጥ ፡ ያመንኩበት ፡ ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አስተማሪዎች ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ አስተማሪዎች ፡ የመተካቱ ፡ ጉዳይ ፡ ያላንዳች ፡ እንከን ፡ በመፈጸሙ ፡ ነው ። ያላንዳች ፡ መሰናክል ፡ የመዘዋወሩን ፡ ጉዳይ ፡ ጫን ፡ አድርጌ ፡ የምናገርበት ፡ ምክንያት ፡ ባለፉት ፡ ቅርብ ፡ ዓመታት ፡ በሌሎች ፡ የአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤቶች ፡ ተመሳሳይ ፡ ለውጥ ፡ ተደርጐ ፡ የመጀመሪያው ፡ ችግር ፡ ከተወጣ ፡ በኋላ ፡ የት/ቤቶቹን ፡ ሥራዎች ፡ ለወራትና ፡

ላመታት ፡ የሚያውክ ፡ ብጥብጥ ፡ ሲደረግ፡ በመመልከቴ ፡ነው ። እነዚህን ፡ የመሳሰሉ፡ ችግሮች ፡ በፊት ፡ አውቀን የ በመዘጋጀታችን ፡ ዕድለኞች ፡ ነን ። ለፋክልቲው ፡ የትምህርት ፡ ዓላማ ፡ ከማናቸውም ፡ ነገር ፡ ተቀዳሚ ፡ ቦታ ፡ (ሥፍራ) የሚሰጡ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አስተማሪዎች ፡ ተባርከናል ።

በፋክልቲው ፡ ውስጥ ፡ የተቀጠሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በሞላ ፡ እዚሁ ፡ ት/ቤት ፡ እንደማይረጉ ፡ ያለፈው ፡ ተመክሮአችን ፡ ቢያስገነዝበንም ፡ የፋክልቲው ፡ አባሎች ፡ ለወደፊቱ ፡ ካለፈው ፡ ይበልጥ ፡ በሥራቸው ፡ እንደሚዘልቁ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ ምክንያቱም ፡ እንዳለፈው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አስተማሪዎች ፡ በመምጣታቸውና ፡ በመመለሳቸው ፡ ነው ። ይህ ፡ እየቀጠለ ፡ የሚሄድ ፡ የአስተማሪዎች ፡ ቋሚነት ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ያስገኛል ። ስለዚህ ፡ ከሦስት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የጠቀስኩትን ፡ (ያገኘሁትን) ችግር ፡ የሚያስወግድ ፡ ጉዳይ ፡ መኖሩ ፡ ያመለክታል ። በያመቱ ፡ አስተማሪዎች ፡ ሥራ ፡ መተውና ፡ መቀያየር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በውጥን ፡ የሚቀሩ ፡ ብዙ ፡ የት/ቤቱ ፡ ሥራዎች፡ነበሩ ። ነባር ፡ አስተማሪዎች ፡ የጀመሩዋቸውን ፡ የሥራ ፡ ውጥኖች ፡ አዲስ ፡ መጪ ፡ አስተማሪዎች ፡ እንዲፈጽሟቸው ፡ ትተውላቸው ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ። አዲስ ፡ መጪዎቹ ፡ የራሳቸውን ፡ አሳብና ፡ ምርምር ፡ ሰውተው ፡ የነበረውን ፡ ጅምር ፡ ሥራዎች ፡ እንዲቀጥሉ ፡ በመደረጋቸው ፡ ሞራላቸው ፡ በማይገባ ፡ አኳኋን ፡ ይፈተን ፡ ነበር ።

## <u>የተጠቃለሉ ፡ ሕጎች ፡ ሥራ ፡ ፍጻሜ ።</u>

ለመጀመሪያዎቹ ፡ ይሰጥ ፡ የነበረውን ፡ አድናቆት ፡ አዲስ ፡ መጪዎቹ ፡ ስለተቀበሉት ፡ ምናልባት ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ተክሰው ፡ ይሆናል ። ለግርማዊ፡ ቀ. ኃ. ሥ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተበረከተውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ <u>የተጠቃለሉ ፡ ሕጎች ፡</u> ይህን ፡ ከመሰሉ ፡ የሥራ ፡ ውጥኖች ፡ (ፕሮጀዎች) አንዱ ፡ ነው ። ከጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ የተጠቃለለ ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ (ጠቃሚ) ሕጎችን ፡ ከመያዙም ፡ በላይ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ከተመሠረተ ፡ ከአሥር ፡ ዓመታት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ ት/ቤቱ ፡ ደክሞበታል ። ሁለቱ ፡ የአማርኛና ፡ ሁለቱ ፡ የእንግሊዘኛ ፡ ቮልዩሞች ፡ ያልተጠቃለሉ ፡ ሕጎችን ፡ በቀላል ፡ መንገድ ፡ አግኝቶ ፡ ለመጠቀም ፡ ያስችላሉ ፡ እኛና ፡ ረዳት ፡ አዘጋጁ ፡ በየነ ፡ አብዲ ፡ ያገኘነው ፡ ምሥጋና ፡ የድሮው ፡ አዘጋጅ ፡ቢል ፡ ኤዊንግና ፡ አሁን ፡ እዚህ ፡ የሌሉ ፡ አያሌ ፡ የፋክልቲው ፡ አባሎች ፡ እዚህ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ተገኝተው ፡ ምሥጋናውን ፡ ቢካፈሉ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ነበር ።

ይህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ <u>የተጠቃለሉ ፡ ሕጎች ፡</u> ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ጠቃሚ ፡ ስጦታ ፡ ነው ። ይህም ፡ ት/ቤታችን ፡ ለአገሪቱ ፡ ሊፈጽምላት ፡ ከሚችለው ፡ አንዱ ፡ ነው ።

ሌሎቹ ፡ የዓመቱ ፡ ታላላቅ ፡ ድርጊቶች ፡ ለምናደርገው ፡ ጥረት ፡ ምስክር ፡ ናቸው፤ ራሳቸውም ፡ አስደናቂ ፡ ናቸው ። አሁን ፡ አሳጥሬ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በዝርዝር ፡ አቀርበዋለሁ ።

## <u>ምርምርና ፡ በሰነድ ፡ መልክ ፡ የመመዝገብ ፡ ፕሮግራሞች ።</u>

የምርምር ፡ደርጋችን ፡ (ኮሚቴአችን) በዚህ ፡ ዓመት ፡ ሁለት ፡ መጻሕፍት ፡ አሳትመዋል ። የመጽሔቱ ፡ አዘጋጆች ፡ አንድ ፡ እትም ፡ አሳትመው ፡ ጨርሰዋል ። በተጨማሪም ፡ ሁለት ፡ እትሞች ፡ እንዲታተሙ ፡ ልከዋል ። እንዲሁም ፡ ለሌላ ፡ እትም ፡ የሚ

ያስፈልገውን ፡ ዝግጅት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ አጠናቀዋል ። ከዚህ ፡ በታች ፡ የሚገለጠው፡ የያንዳንዱ ፡ መምህር ፡ አጭር ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጠቃሚ ፡ በሆኑ ፡ ጥናቶች ፡ እንደሚያተኩር ፡ ያሳያል ።

ዓምና ፡ በእትም ፡ ፕሮግራማችን ፡ የታየው ፡ አስደናቂና ፡ የሚያበረታታ ፡ የገን ዘብ ፡ አያያዝ ፡ መሻሻል ፡ በዚህ ፡ ዓመትም ፡ ቀጥሏል ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ከብዙ ፡ ዓመ ታት ፡ በኋላ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገቢ ፡ አግኝተናል ። ይህ ፡ ዓይነት ፡ መሻ ሻል ፡ ለት/ቤቱ ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ ለማሳተሚያ ፡ የሚሆን ፡ ገን ዘብ ፡ በፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ ላይ ፡ ከመመካት ፡ ያድነዋል ።

እንዲሁም ፡ የንጽጽር ፡ ሕግ ፡ ድርጅታችንን ፡ (Comparative Law Centre) ማጠንከር ፡ ቀጥለናል ። የአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ መስፋፋት ፡ ማዕከላዊ ፡ ድርጅት፡ በፕሮፌሰር ፡ ቫንደርሊንደን ፡ የተሰናዳ ፡ የአፍሪቃ ፡ ሕጐች ፡ መጽሐፍ ፡ ዝርዝር ፡ (African Law Bibliography ፲፱፻፵፯-፲፱፻፷፯) እትሞ ፡ አውጥቷል ። ይህ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ለሕግ ፡ ንጽጽር ፡ (Comparative Law) ጥናት ፡ ከፍተኛ ፡ ጠቃሚነት ፡ አለው ። ማዕከላዊ ፡ ቤተ ፡ መጻፍት ፡ በሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ውስጥ ፡ የአፍሪካ ፡ ሕጐች ፡ ማውጫ ፡ (African Law Digest) ፕሮግራም ፡ ለመጀመር ፡ አድካሚ ፡ የሆነ ውን ፡ የአፍሪቃ ፡ ጋዜጦችና ፡ መጽሔቶች ፡ የመሰብሰብ ፡ ሥራ ፡ ጀምሯል ።

ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ተጀምረው ፡ ከግብ ፡ ያልደረሱ ፡ በሰነድ ፡ መልክ ፡ የመመ ዝገብ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማከናወን ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ እርምጃ ፡ አድርገናል ።

ከሁሉም ፡ ደስ ፡ የሚለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርዶች ፡ ክምችት ፡ ማውጫ ፡ በፋክል ቲው ፡ የበላይ ፡ ጠባቂነት ፡ በሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መዘጋጀቱ ፡ ነው ። አሁን ፡ ታዲያ ፡ ከ፳ሺ ፡ የሚበልጡ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ ለማስተማሪያም ፡ ሆነ ፡ ለጥናት ፡ በቀላሉ ፡ ለማግኘት ፡ ተችሏል ። ለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ማውጫ ፡ ተጀምሮ ፡ ግማሽ ፡ በማለቁ ፡ የአማርኛ ፡ የእንግሊዘኛና ፡ የፈረንሳይኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላቶችን ፡ (Lexicon) ለማ ዘጋጀት ፡ ቀጥታ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ እርምጃ ፡ ተወስዷል ። እንዲ ሁም ፡ በት/ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ጽሑፎች ፡ ከመበላሸት ፡ የሚጠበቁበት ፡ አንድ ፡ ፕሮግራም ፡ አዘጋጅተን ፡ ጨርሰናል ። የጽሑፍ ፡ ግልባጮ ችና ፡ ማባዣዎች ፡ ማውጪያ ፡ አዘጋጅተንላቸው ፡ በሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ አርካይቭ ፡ ውስጥ ይገኛሉ ።

## የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ (ይዞታ) (Academic Standards)

በቅርቡ ፡ በተጀመረው ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ (Senior Thesis) ደንባችን ፡ መሠረት ፡ ለጽሑፍ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ከመስጠት ፡ ይልቅ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ በመስጠታችንና ፡ ጸሐፊው ፡ በሦስት ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ የጻፈውን ፡ እንዲያብራራ ፡ በመደረጉ ፡ ተማሪውቹ ፡ የአገሪቱን ፡ ችግሮች ፡ በጥልቅ ፡ እንዲመረምሩ ፡ ዕድል ፡ ሰጥ ቷቸዋል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ለዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ያጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ በተቀዳሚ፡ ለማስተማር ፡ አንድ ፡ ዝግጅት ፡ አስፈላጊ ፡ ቢሆንም ፡ ተማሪዎቹ ፡ አዲሱን ፡ ለውጥ ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ሰርተውበታል ። ከአምስት ፡ ጐረቤት ፡ አገሮች ፡ የመጡ ፡ ምሁራ ንና ፡ ፈታኞች ፡ እንግዶቻችን ፡ ስለጽሑፎቹ ፡ ከፍተኛ ፡ ይዞታ ፡ (ደረጃ) ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ አስደስቶናል ።

የት/ቤታችን ፡ ከፍተኛ ፡ የትምህርት ፡ ይዞታ ፡ የሚያሳይ ፡ ሌላው ፡ ምልክት ፡ ደግሞ ፡ በዋሽንግተን ፡ ዲሲ ፡ በተደረገው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ክርክር ፡ ውድ ድር ፡ ቡድኖችን ፡ የፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ነው ። በብርሃን ፡ ጊላና ፡ በአስፋ ፡ ጫቦ ፡ እን

ዲሁም ፡ በኤልያስ ፡ ኑሪ ፡ (በተጠባባቂነት) የተመሠረተው ፡ ቡድናችን ፡ እንደ ፡ እም ናው ፡ ብዙ ፡ ሽልማቶች ፡ ባያገኝም ፡ በጠቅላላ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ውጤትን ፡ ካመጡ ፡ ቡድ ኖች ፡ አንዱ ፡ ነበር ። በጠቅላላው ፡ ካሥር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወዳዳሪ ፡ ብድኖች ፡ የአ ራተኛነት ፡ ቦታ ፡ ሲይዝ ፡ በጽሑፍ ፡ ማቅረብ ፡ ሦስተኛ ፡ እንዲሁም ፡ ብርሃን ፡ ጊላ፡ በቃል ፡ ንግግር ፡ ሁለተኛ ፡ ሆኗል ።

ይህን ፡ ዓይነቱን ፡ ግሩም ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት ፡ የበቃነው ፡ በዩኒቨርሲቲያችን ፡ በምንሰጣቸው ፡ ከባድ ፡ ውድድሮች ፡ መሆኑ ፡ ይሰማል ። ባለፉት ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ በአፍሪካ ፡ በኢስያ ፡ ባውሮፓና ፡ በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙ ፡ የታወቁ ፡ የሕግ ፡ ት/ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ያሳየነው ፡ የውድድር ፡ ብልጫ ፡ በሕግ ፡ ት/ቤታችን ፡ ላይ ፡ ያለንን ፡ እምነት ፡ ከማጠንከሩም ፡ በላይ ፡ ለአንድ ፡ ታታሪ ፡ ት/ቤት ፡ የሚያስፈልገውን የሞ ራል ፡ ድጋፍ ፡ ሰጥቶናል ።

## ተማሪዎች ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎችና ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ።

የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በጠቅላላው ፡ ሊሳተፉበት ፡ ባይችሉም ፡ አንዳንድ ፡ ማኅበ ራዊ ፡ ስብሰባዎችን ፡ አድርገናል ፡ (የተማሪዎቹ ፡ ቁጥር ፡ ያልተሟላበት ፡ ምክንያት ፡ ተማሪዎቹ ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ ወጥተው ፡ እስከ ፡ ሁለተኛው ፡ ሰሚስተር ፡ ባለመመለ ሳቸው ፡ ነበር) ። እንዲሁም ፡ ለቀድሞ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ሁለት ፡ ዓቢይ ፡ ሥራዎች ፡ ሰጥተናል ። ግን ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ጠቃሚ ፡ ሆኖ ፡ ያገኘነው ፡ ድርጊት ፡ አንድ ፡ የቀ ድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ቡድን ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ረዳት ፡ ኮሚቴ ፡ ተቋ ቁሞ ፡ ውሳኔ ፡ ያልተደረገላቸው ፡ የመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ችግሮች ፡ መፍትሔ ፡ እንዲገኝ ላቸው ፡ ሐሳብ ፡ በማቅረብ ፡ ተማሪዎቹን ፡ መርዳት ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ አሁን ፡ ስለመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ አሳሳቢ ፡ የሆኑ ፡ ችግሮች፡ ባይገጥሙም ፡ ለወደፊቱ ፡ ስለመኖሪያ፡ ቤቱ ፡ አጠቃቀም ፡ ሊነሱ ፡ የሚችሉት ፡ ችግሮችን ፡ ለማስወገድ ፡ ከተማሪዎች ፡ ዲንና፡ ከዩኒቨሲቲው ፡ አስተዳደር ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ጋር ፡ በመነጋገር፡ አንድ ፡ ጠቃ ሚ ፡ ደንብ ፡ ማውጣት ፡ የሚበጅ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተነዋል ። ያለዚህ ፡ መምሪያ ፡ ደንብ ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤትን ፡ ልዩ ፡ አቋም ፡ የሚያውቅ ፡ ሕግ፡ ስለማይኖር ፡ አንዳንድ ፡ ችግሮች ፡ በተነሱ ፡ ቁጥር ፡ ችግሮቹን ፡ ሊያጋንኑ ፡ ይችላሉ ። ይህ ፡ ስምም ነት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ተጠናቋል ። ለዚህም ፡ የቀድሞና ፡ የአሁን ፡ ተማሪዎቻችን ፡ እንዲሁም ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ አስተዳደር ፡ ላሳዩት ፡ ትብብር ፡ አመሰግናቸዋለሁ ። ንቁ ፡ የሆነ ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ለመመሥረት ፡ እንዲሁ ፡ ዓይነቱ ፡ በቀድሞ ፡ ተማሪዎችና ፡ በት/ቤቱ ፡ ዘላቂ ፡ የሆነ ፡ ግንኙነት ፡ መመሥረቱ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ይሰ ማናል ። አንድ ፡ አነስተኛ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ በሰይ ፍና ፡ ሚዛን ፡ የተንቆጠቆጠ ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ዩ. የሚሉ ፡ ፊደላት ፡ ያለበት ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት መለዮ ፡ ክራቫት ፡ ተቀባይነት ፡ ማግኘቱ ፡ ነው ።

## የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ።

የዩኒቨርስቲውን ፡ አጠቃላይ ፡ ፕላን ፡ በመከተል ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴርና ፡ ከሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ አንድ ፡ ኮሚቴ ፡ አቋቁሟል ። ይህ ፡ ኮሚቴ ፡ የተመሠረተው ፡ የምሩቅ ፡ ተማሪዎች ፡ ተፈላጊ ነትና፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የመቅጠር ፡ ኃይል ፡ ተመዝኖ ፡ እንዲሁም ፡ ለሚመጡት ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ከዚያም ፡ አልፎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ትምህርትን ፡ ለማስፋፋት፡ ባለው፡ እቅድ ፡ ላይ ፡ ነው ።

መግለጫው ፡ ጉልህ ፡ ስለሆነ ፡ ማብራሪያ ፡ አያሻውም ። በጽሑፍ ፡ የተደገፈና ፡ ፍቱን ፡ የሆነ ፡ ክርክር ፡ የያዘ ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ ወደፊት ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ ላይ ፡ ሐሳቡን ፡ የጣለ ፡ ሁሉ ፡ እንዲያነበው ፡ አሳስባለሁ ። መግለጫው ፡ ያተኮረው ፡ በቁጥር ፡ ብዛት ፡ ሳይሆን ፡ በዓይነት ፡ (በጥራት) ነው ። መግለጫው ፡ በመጠኑ ፡ የሕግ ፡ ምሩቃን ፡ቁጥር ፡ እንዲጨምር ፡ ያሳስባል ። እውነተኛው ፡ ተፈላጊ ፡ ነገር ፡ የቁጥር ፡ መብዛት፡ ሳይሆን ፡ ለታዳጊ ፡ አገር ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ የሚያደረጅ ፡ ትጉህና ፡ ታታሪ ፡ የሆኑ ፡ ምሩቃን ፡ በዲግሪም ፡ ሆነ ፡ ከዚያም ፡ በታች ፡ ማስመረቅ ፡ ነው ።

የታወቁ ፡ የሕግ ፡ ምሁራን ፡ በኬንያ ፡ በሱዳን ፡ ታንዛንያ ፡ ዩጋንዳና ፡ ዛምቢያ ፡ ከሚገኙት ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መጥተው ፡ ጐብኝተውናል ። ጉብኝቱም ፡ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ ከተደረጉት ፡ ጉልህ ፡ ሁኔታዎች ፡ አንዱ ፡ ነበር ።እንግዶቹም ፡ ሆኑ ፡ እኛ ፡ አስተናጋጆች ፡ ከጉብኝቱ ፡ ጥቅም ፡ ማግኘታችን ፡ ተሰምቶናል ። በተለይም ። በአካዳሚ ፡ ፕሮግራማችን ፡ ላይ ፡ ጐብኝዎቹ ፡ የሰጡት ፡ ግምገማ ፡ ለወደፊት ፡ ጠቃሚ፡ ይሆናል ።

ጥሩና፡ መልካም ፡ የሆነ ፡ አቅዳችን ፡ ከፎርድ ፡ ድርጅት ፡ በሚያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ይካሄድ ፡ የነበረውን ፡ ፕሮግራማችንን ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይህንኑ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ፈቃደኞች ፡ ሆነው ፡ እንዲገኙ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ በአለፉት ፡ አራት ፡ ዓመታት ፡ ከድርጅቱ ፡ እናገኝ ፡ ከነበረው ፡ ሰፊ ፡ የገንዘብ ፡ ችሮታ ፡ የተነሣ ፡ በቅርቡ ፡ ችግር ፡ እንደማይገጥመን ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ሐሳባችን ፡ ግን፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፕሮግራም ፡ በገንዘብ ፡ እጥረት ፡ ለወደፊቱ ፡ እንዳይታወክ ፡ ደህና ፡ ተቀማጭ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ነበር ። የዩኒቨርሲቲው ፡ ሹማምንት ፡ የአሳዩት፡ መተባበርና ፡ መግባባት ፡ ለሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ የወደፊት ፡ ትልም ፡ ጠንካራ ፡ መሠረት ፡ ሆኖአል ።

አሁን ፡ የዓመቱን፡ ክንውኖችና ፡ ከላይ ፡ ላልተጠቀሱት ፡ ሥራዎች ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ መረጃዎችና ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫዎች ፡ አቀርባለሁ ።

## ስለ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ አጠቃላይ ፡ መረጃ

### የአካዳሚክ ፡ ኮሚስዮን ፡

ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በአካዳሚ ፡ ኮሚስዮን ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ቁጥር ፡ በልጦ ፡ ታይቶአል ። ብዙ ፡ ስብሰባዎች ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትንና ፡ መመሪያዎችን ፡ በማጤን ፡ በመልካም ፡ ሁናቴ ፡ ተፈጽመዋል ። ከሥራቸው ፡ ይሰናበቱ ፡ የነበሩት ፡ ረዳት ፡ ዲን ፡ ሚስተር ፡ ጆን ፡ ኤዲ ፡ የአካዳሚክ ፡ ኮሚስዮን ፡ ፀሐፊነታቸውንና፡ ሌሎች ፡ ተግባራቸውን ፡ ጭምር፡ ለረዳት ፡ ዲን ፡ አቶ ፡ ወርቁ ፡ ተፈራ ፡ ሲያረካክቡ ፡ ነበር ። በዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ገደማ፡ ሚስተር ፡ ጆን ፡ ኤዲ ፡ ለረዳት ፡ ዲንና ፡ ለአካዳሚክ ፡ ኮሚስዮን ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ወደፊት ፡ መሻሻል ፡ የሚገባቸው ፡ የሥራ ፡ መመሪያዎችንና ፡ የአሠራር ፡ ልማዶችን ፡ የያዙ ፡ ማስታወሻዎች ፡ አዘጋጅተው ፡ አስረክበዋል ።

በዓቢይ ፡ ውሳኔዎች ፡ ረገድ ፡ ኮሚስዮኑ ፡ በፋክልቲው ፡ ሙሉ ፡ ስብሰባ ፡ የተወሰኑትን ፡ ውሳኔዎች ፡ መከተል ፡ ቀጥሏል ።

ተማሪዎች ።

በሺህ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አምስት ፡ ዓ. ም. (እ. አ. .አ ፲፱፻፸፪.፸፫) ለኤል. ኤል. ቢ. ፕሮግራም ፡ የተመዘገቡት ፡ ተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ።

| በአንደኛው ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ.ም. | በሁለተኛው ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም. |
| --- | --- |
| የቀን ፡ ፸፫ | የቀን ፡ ፻፵፬ |
| የማታ ፡ ፹፰ | የማታ ፡ ፸፬ ፡ |

በሁለተኛው ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ የቀን ፡ ተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ መበርከት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ በአለፈው ፡ ዓመት ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ ወጥተው ፡ የነበሩት ፡ ተማሪዎች፡ በመመለሳቸው ፡ ነው ። በአንደኛው ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ ማለቂያ ፡ ከ፸፫ ፡ ተማሪዎች፡ መካከል ፡ አርባው ፡ ሊዲን ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ሲበቁ ፡ አራቱ ፡ በማስጠንቀቂያ ፡ ሁለቱ ፡ በማሻሻያ ፡ ሲያልፉ ፡ አሥሩ ፡ ስለወደቁ ፡ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ተሰናብተዋል ። ከተሰናበቱት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ከሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ የማታ ፡ ተማሪዎች ፡ መካከል ፡ ነበሩ ። በሁለተኛው ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ ማለቂያ ፡ ሰላሳ ፡ አምስት ፡ ተማሪዎች ፡ ለዲን ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ በቅተዋል ፤ ሰላሳ ፡ ስድስት ፡ ተማሪዎች ፡ በማስጠንቀቂያ ፡ ስድስት ፡ ደግሞ ፡ በማሻሻያ ፡ ሲያልፉ ፡ አራት ፡ ስለወደቁ ፡ ከትምህርት ፡ ቤቱ፡ ተሰናብተዋል ። በአካዳሚክ ፡ ይዞታቸው ፡ ተዳክመው ፡ የነበሩ ፡ ሰባት ፡ ተማሪዎች ፡ ደግሞ ፡ ደህና ፡ አቋም ፡ አግኝተዋል ። ሰላሳ ፡ አራት ፡ ተማሪዎችን ፡ በባችለር ፡ ዲግሪ ፡ በማስመረቃችን ፡ ደስ ፡ ተሰኝተናል ። ከእነርሱም ፡ ሁለቱ ፡ የተመረቁት ፡ በማዕረግ ፡ ነው ።

ፋክልቲው ፡ በሁለቱም ፡ የትምህርት ፡ ወቅቶች ፡ ፪፻፴፭ ፡ ተማሪዎች ፡ በዲፕሎም ፡ ፕሮግራም ፡ ሲኖሩት ፡ በሰኔው ፡ የምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፻፹፱ ፡ ተማሪዎች፡ በሕግ ፡ ዲፕሎም ፡ አስመርቋል ። እነዚሁ ፡ ተማሪዎች ፡ የተዋጣለት ፡ ግብዣ ፡ ከማድረጋቸውም ፡ በላይ ፡ በሲንየር ፡ ሴምናር ፡ አዳራሽ ፡ የሚታየውን ፡ ባለደወል ፡ የግርግዳ ፡ ሰዓት ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አበርክተዋል ።

ከተማሪዎቹ ፡ መመለስ ፡ የተነሳ ፡ ብዛቱ ፡ ያልተለመደ ፡ የተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ (ወደ ፡ ፵፰ ፡ የሚጠጋ) ለብሔራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ፕሮግራም ፡ በቅተዋል ። ቢሆንም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሚኒስትሮች ፡ መተባበር ፡ እያንዳንዱን ፡ ተማሪ ፡ በሕግ ፡ ጠቀስ ፡ ሥራ ፡ ላይ፡ ለማዋል ፡ አንዳችም ፡ ችግር ፡ እንደማይኖር ፡ ተስፋ ፡ አሳድሮአል ።

## የአስተማሪና ፡ የተማሪ ፡ ግንኙነት ።

ለአምስት ፡ ዓመታት ፡ በተከታታይ ፡ በፖለቲካ ፡ ምክንያት ፡ በተማሪዎቹ ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ መወገድና ፡ ወደትምህርት ፡ እንዲመለሱ ፡ ለማድረግ ፡ በነበረው ፡ ችግር ፡ የተነሣ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ በየጊዜው ፡ እክል ፡ ይገጥመው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ እስኪጀመር ፡ በሕግ ፡ ትምህርት፡ ቤት ፡ የነበሩን ፡ ተማሪዎች ፡ ለወትሮው ፡ ከነበሩት ፡ ሙሉ ፡ ተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ ወደ ገሚሱ ፡ የሚጠጋው ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ ድርጊቶቹን ፡ በከበበው ፡ ኃልይ ፡ የስሜት ፡ ፍላት ፡ ውስጥ ፡ የአካዳሚውን ፡ ፕሮግራም ፡ የሚያዳብር ፡ መልካም፡ ያስተማሪና ፡ የተማሪ ፡ ግንኙነት ፡ መመሥረት ፡ ቀላል ፡ አልነበረም ። የመምህራኑና ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ ከሆኑ ፡ ተማሪዎች ፡ በስተቀር ፡ በአካዳሚው ፡ እድል ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ለመጠቀም ፡ ፍቃደኛ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ የሚያበረታታ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ።

ለዚህ ፡ ግብ ፡ የሚውሉ ፡ አያሌ ፡ ሐሳቦች ፡ ባለፉት ፡ ጊዜያት ፡ በአንክሮ ፡ ተና ግሬ፡ ነበር ። ወደፊትም ፡ እዚህ ፡ ስለማልገኝ ፡ ልደግማቸው ፡ አልችልምና ፡ ሁሉቱን ፡ መሠረታዊ ፡ ነጥቦች ፡ ባጭሩ ፡ ለመናገር ፡ ይህን ፡ ዕድል ፡ ልጠቀምበት ፡ እሻለሁ ።

የመጀመሪያው ፡ ነጥብ ፡ እንደሌሎቹ ፡ መሠረታዊ ፡ ነጥቦች ፡ ሁሉ ፡ ከቡዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ሴኔካ ፡ በተባለው ፡ ሮማዊ ፡ ገጣሚ ፡ በማጋነን ፡ የተነገረ ፡ ነበር ። እሱ ፡ እንዳስመለከተው ፡ "ችግሩ ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ አለማግኘቱ ፡ ሳይሆን ፡ ባለን ፡ ጊዜ ፡ አለአግባብ ፡ መጠቀማችን ፡ ነው ።" ተማሪዎቻችንም ፡ የየግል ፡ የየዕለት ፡ ሰዓታት፡ አጠቃቀማቸውን ፡ በጥሞና ፡ ሲያስቡ ፡ ካሁኑ ፡ ይበልጥ ፡ ለማከናወን ፡ እንደሚችሉና ፡ የሕግ ፡ ትምህርታቸውንም ፡ ጠንቅቆ ፡ ለማወቅ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚኖራቸው ፡ ተገንዝበ ዋል ።

የሚቀጥለው ፡ ሐሳብ ፡ ደግሞ ፡ የሕግ ፡ ትምህርትን ፡ ጠንቅቆ ፡ ለማወቅ ፡ የሚ ደረገው ፡ ብርቱ ፡ ሙከራ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ሰር ፡ ኤድዋርድ ፡ ኮክ ፡ እንደ ጻፈው ፡ "የታወቀው ፡ የሕግ ፡ እርግጠኛነት ፡ ታላቅ ፡ የሕግ ፡ ደኅንነት ፡ ነው ።" ይህም ፡ ማለት ፡ የታወቁ ፡ ሕጐችና ፡ ቋሚ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ባሉበት ፡ ሰዎች ፡ በሥልጣ ናቸው ፡ የዝንባሌያቸው ፡ ባርያ ፡ ከሚያደርጉን ፡ ነፃ ፡ እንሆናለን ። በድንጋጌዎች ፡ ካል ተገቱ ፡ በቀር ፡ በልብ ፡ መሻት ፡ በቁጥጥራቸው ፡ ውስጥ ፡ ያውሉናል ። ይህ ፡ ግን ፡ ሕግ ፡ ሁልጊዜ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይደለም ። አናቶል ፡ ፍራንስ ፡ እንደጻፈው ፡ "ሕግ፡ ገናና ፡ በሆነ ፡ እኩልነት ፡ መንፈስ ፡ ሀብታሙንም ፡ ሆነ ፡ ደሀውን ፡ በየድልድዩ ፡ሥር ፡ ከመተኛት ፡ በየመንገዱ ፡ ከመለመንና ፡ ከመስረቅ ፡ ይከለክላል ።" የዚህ ፡ ስሜት ፡ አባባል ፡ ከዚህ ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ማለትም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሥርዓት ፡ ሕጐች ፡ ቢኖሩም ፡ በበለጠ ፡ ቅንና ፡ ትክክለኛ ፡ ለመሆን ፡ አይችሉም ፡ ማለት ፡ አይደለም ።

ጻሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ አንዳንድ ፡ ተማሪዎች ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች እንዳሉት ፡ ይዘነጋሉ ። እነዚሁም ፡ የሕጐችን ፡ ሥርዓት ፡ መፍጠርና ፡ ማዘጋጀት ፡ እንዲሁም ፡ ከመጀመሪያው ፡ የሚስማማው ፡ ሕጐችን ፡ ማሻሻልና ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡መዋ ላቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ ናቸው ። አንዳንድ ፡ ተማሪዎች ፡ በሕጉ ፡ ወይም ፡ በአሠራሩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ጉድለቶች ፡ እየጠቆሙ ፡ ሕግ ፡ ማጥናት ፡ ፋይዳ ፡ የለውም ፡ ይላሉ። ይህ ፡ በጣም ፡ ግራ ፡ የተጋባ ፡ አስተያየት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በሂሳብ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ሌሎችን ፡ ስለሚያጭበረብሩ ፡ ሂሳብ ፡ ማጥናት ፡ ዋጋ ፡ የለ ውም ፡ ከሚለው ፡ አስተያየት ፡ የተለየ ፡ አይደለም ። የሕግ ፡ ጥበብ ፡ በቀላሉ ፡ የሚገኝ፡ አይደለም ፡ ተማሪዎቹም ፡ ይህንን ፡ ጥበብ ፡ ለማግኘት ፡ ያላቸው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ውስን ፡ ነው ። ጥሩ ፡ የሕግ ፡ አዋቂ ፡ ሕጉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውልበትን ፡ የኅብረተሰቡን፡ ሁናቴ ፡ ማወቅና ፡ የተሻለ ፡ ለውጥ ፡ ለማድረግ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ ለታላቅ ፡ ፍትሕ ፡ የሚያልም ፡ ሰው ፡ ዕድል ፡ በገጠመው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ሐሳቡን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ይገባዋል ። ታዲያ ፡ የሕግ ፡ ጥበብ ፡ ካላተረፈ ፡ ከሕ ልሙ ፡ ሲነቃ ፡ እራሱ ፡ አንዳችም ፡ ኃይል ፡ እንደሌለው ፡ ይረዳል ።

መምህራኑ ፡ በተማሪዎቹ ፡ የረሀብ ፡ ማስወገጃ ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ተባባሪ ፡ ሆነዋል ። እኔም ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ጊዜያዊ ፡ ኮሚቴ ፡ በአቶ ፡ ፍቅሬ ፡ መርዕድ ፡ የተቋ ቋመውን ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ክፍል ፡ ከተቀዳሚዎቹ ፡ አዋጪዎች ፡ አንዱ አድርጎ ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ስሙን ፡ ማስነሳቱን ፡ ስገልጽ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

በዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ የተለያዩ ፡ የትምህርት ፡ ክፍለጊዜ ፡ መርሐ ፡ ግብሮችን ፡ ለመቀበል ፡ ፈቃደኞች ፡ ያላደረጋቸው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በተለይም ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ የነበራቸው ፡ የከፊል ፡ የሥራ፡

መርሐ ፡ ግብር ፡ እንደነበረ ፡ አውቀናል ። የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ይህንን ፡ ካጠና ፡ በኋላ ፡ የሚከተለውን ፡ ወስኗል ። ከአካዳሚው ፡ ፕሮግራም ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ትምህርትን፡ በግብር ፡ መግለጽ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የሚደገፍና ፡ ለብሔራዊ ፡ አገልግሎች ፡ እንደሚ ደረገው ፡ ሁሉ ፡ ግብሩን ፡ ከትምህርቱ ፡ ጋር ፡ በሚገባ ፡ ልናካሄደው ፡ ተገቢያችን ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ተጨማሪ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ለጥቂት ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ እንደ ማንቀበል ፡ ወይንም ፡ የቀን ፡ ተማሪዎቻችንን ፡ የትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ቅጥሮች ፡ አድርገን ፡ ልንመለከታቸው ፡ እንደማንወድ ፡ ወስነናል ። ያው ፡ ትክክለኛው ፡ የትምህርት ፡ ይዞታ፡ አሁንም ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ ይሠራበታል ።

ብዙ ፡ የጥንት ፡ ሆነ ፡ አሁን ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ተማሪዎች ፡ ለነፃ ፡ ትም ህርት ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ ያቀረቡት ፡ ማመልከቻ ፡ የመምህራኑን ፡ ድጋፍ ፡ ሽተው ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ተቃንቶላቸዋል ። አመልካቾቹ ፡ ራሳቸው ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ብቁ ፡ ሆነው ፡ ባይገኙ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ የተገኘው ፡ ውጤት ፡ በጣም ፡ ባስደነቀ ፡ ነበር ።

ይህን፡ የነፃ ፡ ትምህርት ፡ ያገኙ ፡ እንዳርጋቸው ፡ ጥሩነህ ፡ በብሪታንያ ፡ ቆንሲል ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፤ ዳንኤል ፡ ኃይሌ ፡ ወደ ፡ ሀርቫርድ ፡ ዳዊት ፡ ወልደ ጊዮርጊስ ፡ ወደ ፡ ኮሎምቢያ ፡ ጌታቸው ፡ ሻረው ፡ ወደ ፡ ማጊል ፡ ጉሹ ፡ ወልዴ ፡ ወደ ዬል ፡ ኃይሌ ፡ ከበደ ፡ ወደ ፡ ዬል ፡ ሕዝቅያስ ፡ አሰፋ ፡ ወደ ፡ ኖርዝዌስተርን ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡ በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ የነፃ ፡ ትምህርት ፡ እርዳታ ፡ ፕሮግራም ፡ በኩል ፡ ምናልባት ፡ ወደ ፡ እስታንፎርድ ፤ ሽፈራው ፡ ወ/ሚካኤል ፡ ወደ ፡ ኮሎምቢያ ፡ ናቸው ።

እኔና ፡ ሌሎች ፡ የሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ አባሎች ፡ ለሁሉም ፡ ባይሆን ፡ ለጥቂቶች ፡ የቀ ንና ፡ የማታ ፡ ተማሪዎች ፡ ግብዣ ፡ አድርገናል ። እንዲሁም ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ ሹማም ንት፡ እርዳታ ፡ ለምሩቃኑ ፡ የመሰነባበቻ ፡ ግብዣ ፡ አድርገናል ።

በዓመቱ ፡ ማለቂያ ፡ ላይ ፡ ከትምህርቱ ፡ ፕሮግራም ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ የፈተና ፡ አጻጻፍ ፡ (አመላለስ) ዘዴ ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ ዝግጅት ፡ አቅርቤ ፡ ወደ ፡ ሰላሳ ፡ የሚጠጉ፡ ተማሪዎች ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ ነበር ።

## <u>መምህራን ።</u>

በዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ሃያ ፡ አንድ ፡ ቋሚ ፡ መምህራንና ፡ ሁለት ፡ ከፈረን ሣይ ፡ የመጡ ፡ የበጐ ፡ ፈቃድ ፡ ልኡካን ፡ ነበሩን ። አምስቱ ፡ አዳዲስ ፡ አስተማሪዎች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ነበሩ ። እያንዳንዳቸውም ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ አስተዳደር ፡ ጋር ፡ ተጨ ማሪ ፡ ድርድር ፡ ያሻው ፡ ስለነበረ ፡ የየግል ፡ የሥራ ፡ ውላቸው ፡ የተለየ ፡ ሐሳብ ፡ ነበ ራቸው ። ዕድል ፡ ሆኖ ፡ የቀሩዋቸው ፡ ድርድሮች ፡ በሚገባ ፡ ተከናውነዋል ።

በሁለተኛው ፡ የትምህርት ፡ ወቅት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ መምህራን ፡ የማስተማር ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ፡ ተፈጽመዋል ። ዶክተር ፡ ላንግ ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ሲመለሱ ፡ አቶ ፡ ሠመረ ፡ አብ ፡ ሚካኤል ፡ ወደግል ፡ ሥራ ፡ ተሰማርተዋል ። ዶክተር ፡ ቨርሄልስት ፡ ደግሞ ፡ በቤልጅግ ፡ መንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ ወደሌላ ፡ ሥፍራ ፡ መሄድ ፡ ሲችሉ ፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ በአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ማእከላዊ ፡ ድርጅት ፡ ሥራ ፡ ለመቀጠል ፡ እዚሁ ፡ ቀርተዋል ።

ት/ቤቱ ፡ አራት ፡ ሰዎችን ፡ ለሹመት ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። እኔም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ለሹመት ፡ የተገቡ ፡ ለመሆናቸው ፡ እርግጠኛ ፡ ነበርሁ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሹመታቸው ፡ ከመጽደቁ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ሥነ ፡ ሥረዓታዊ ፡ ችግሮች ፡ ገጥመውን ፡ ነበር ። ሹመታቸውም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

አቶ ፡ ዳንኤል ፡ ኃይሌ ፡ ከረዳት ፡ ሌክቸረርነት ፡ ወደሌክቸረርነት ።

አቶ ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፡ አቶ ፡ ወርቁ ፡ ተፈረና ፡ ዶክተር ፡ ቲየሪ ፡ ቬርሄልስት ፡ ከሌክቸረርነት ፡ ወደረዳት ፡ ፕሮፌሰርነት ፡ ከፍ ፡ ብለዋል ።

## በውጭ ፡ አገር ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ የሚገኙና ፡ አዳዲስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ።

አቶ ፡ አቢዩ ፡ ገለታ ፡ በሀርቫርድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሚሰጠውን ፡ የሕግ ፡ የማስተር ፡ ዲግሪ ፡ ፕሮግራም ፡ በሚገባ ፡ ፈጽመዋል ። ወደዚህ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤትም ፡ ይመለሳሉ ። ልቀበላቸው ፡ እዚህ ፡ ልገኝ ፡ ባለመቻሌ ፡ ቅር ፡ እሰኛለሁ ። እዚህ ፡ እንደመጣሁ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ የንብረት ፡ ሕግ ፡ ለማስተማር ፡ ከፊሉን ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ በተካፈልኩበት ፡ ጊዜ ፡ ከማውቃቸው ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ መምህራን ፡ አንደኛው ፡ ሆነው ፡ አግኝቼአቸዋለሁ ።

ት/ቤቱ ፡ በ፲፱፻፷፮ ፡ (፲፱፻፸፫/፸፬) ፡ ዓ. ም. ሥራቸውን ፡ የሚጀምሩ ፡ አራት ፡ እጩ ፡ መምህራን ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። እነርሱም ፡ አሌክሳንድራ ፡ ሀማዊ ፡ ተስፋዬ ፡ ወ/ጻድቅ ፡ ወንድወሰን ፡ መክብብና ፡ አንዳርጋቸው ፡ ጥሩነህ ፡ ሲሆኑ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከዚህ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከ፫ ፡ ነጥብ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አጠቃላይ ፡ ውጤት ፡ የተመረቁ ፡ ናቸው ። እያንዳንዳቸውም ፡ ለት/ቤቱ የተለየ ፡ አገልግሎት ፡ እንደሚያበረክቱ ፡ እናምናለን ።

## አዲሱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዲንና ፡ የመምህራን ፡ አመራረጥ ፡ ዘዴ ።

አዲሱ ፡ ዲን ፡ አቶ ፡ ወርቁ ፡ ተፈራ ፡ ይሆናሉ ። በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያላቸው ፡ የሥራ ፡ ልምምድና ፡ የአስተዳደር ፡ ችሎታ ፡ እንዲሁም ፡ በየጊዜው ፡ ያሳዩት ፡ ጥበብና ፡ ብልህነት ፡ አሁንም ፡ ለዩኒቨርሲቲውና ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በሚገባ ፡ እንደሚጠቅም ፡ አምናለሁ ። የማስተር ፡ ድግሪአቸውን ፡ ባገኙበት ፡ በኖርዝ ፡ ዌስተርን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ያላቸው ፡ ጥሩ ፡ ውጤትና ፡ በቅርቡ ፡ ለረዳት ፡ ፕሮፌሰርነት ፡ ያገኙት ፡ ሹመት ፡ ያላቸውን ፡ የምሁር ፡ ተወህቦ ፡ ያረጋግጣል ።

*ሀ.* የቀድሞው ፡ የአካዳሚክ ፡ ዓመት ፡ ከማለቁ ፡ አስቀድሞ ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ. ም. (፲፱፻፸፫-፲፱፻፸፬) የመጀመሪያውን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዲን ፡ ለመሰየም ፡ ተስማሚ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚሆን ፡ ጽኑ ፡ እምነቴን ፡ በገሃድ ፡ አስታውቄ ፡ ነበር ።

በዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ አብዛኛውን ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ መምህራን ፡ በዚሁ ፡ አስተያየት ፡ ተስማምተው ፡ ነበር ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከውጭ ፡ በተለይም ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ከዩኒቨርሲቲውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተቃውሞ ፡ ነበር ። በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ያሉትን ፡ ሠራተኞች ፡ ሌሎችንም ፡ ሰዎች ፡ ዲን ፡ የሚሆን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ለመምረጥ ፡ አስተያየታቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ጠይቄአቸው ፡ ነበር ።

የያንዳንዱንም ፡ አስተያየትና ፡ ሐሳብ ፡ በሚገባ ፡ ተከታትለነዋል ። ከዩኒቨርሲቲው ፡ ውጭ ፡ ከሆኑ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይመረጥ ፡ የሚሉ ፡ ጥቂት ፡ አስተያየቶች ፡ ሲቀርቡ ፡ አንድ ፡ አስተያየት ፡ ደግሞ ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አባሎች ፡ ውስጥ ፡ ይሰየም ፡ የሚል ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ከጥናታችን ፡ ባገኘነው ፡ ውጤት ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ ውጭ ፡ ካሉት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ሙሉ ፡ ጊዜውን ፡ ሰጥቶ ፡ ዩኒቨርሲቲውን ፡ ለማገልገል ፡ የሚችል ፡ ባለመገኘቱ ፡ ከውጭ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እና ፡ ከኛው ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ምርጫ ፡ የማድረጉ ፡ ጉዳይ ፡ ሊነሣ ፡ አልቻለም ። ከሕግ ፡ ትምህ

ርት ፡ ቤቱ ፡ አባሎች ፡ ለሹመቱ ፡ የታጩት ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ማለት ፡ አቶ ፡ ወርቁ ፡ ተፈራ ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱም ፡ ዲን ፡ እንዲሆኑ ፡ በሰኔ ፡ አረጋገጠ ። በኋላም ፡ የዩኒቨርስቲው ፡ አስተዳደር ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዲን ፡ ለመሾም ፡ ጊዜው ፡ መድረሱን ፡ ተስማማበት ። ፕሬዚዳንቱም ፡ በአቶ ፡ ወርቁ ፡ ለስፍራው ፡ ሁነኛነት ፡ በመስማማታቸው ፡ ስማቸውን ፡ ለአስተዳደር ፡ ቦርድ ፡ (Board of Governors) አስተላለፉ ።

ባለፈው ፡ መግለጫዬ ፡ የገለጽሁት ፡ አዳዲስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ የሚሰየሙበት ፡ እረጅሙ ፡ የምርጫ ፡ አካሄድ ፡ በዚህም ፡ ዓመት ፡ ሲቀጥል ፡ በመጨረሻው ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ደንበኛ ፡ የምርጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ታክሎበት ፡ ነበር ። የእያንዳንዱ ፡ ዕጩ ፡ የተሟላ ፡ ዶሴ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ስለነበረ ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆኑ ፡ መምህራን ፡ ሁሉ ፡ መርምረዋቸው ፡ ነበር ። ከመምህራኑ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ድምፅ ፡ ሰጥተዋል ። ውጤቱም ፡ አራት ፡ የተዋጣላቸው ፡ ምርጫ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ተመራጮችም ፡ በሥራ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ድጋፍ ፡ የሚደሰቱ ፡ መምህራን ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ።

ለሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ የሚያገለግሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መምህራን ፡ አመራረጥ ፡ ለመጠየቅ ፡ ጉዳይ ፡ ዲኑ ፡ ዘንድ ፡ ከመቅረባቸው ፡ በቀር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ አነስተኛ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ አመራረጡ ፡ ሙሉ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ስሜት ፡ ጨምሯል ። ዶሴያቸውን ፡ ብቻ ፡ በመመልከት ፡ ብያኔ ፡ ማሳለፉ ፡ ለመምህራኑ ፡ የበለጠ ፡ ችግር ፡ ቢሆንባቸውም ፡ ከመምህራኖቹ ፡ ቁጥር ፡ ከግማሽ ፡ በላይ ፡ ዶሴአቸውን ፡ ለማጥናት ፡ ጊዜ ፡ ከወሰዱ ፡ በኋላ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ለግሰዋል ፤ እኔም ፡ እንደእውነቱ ፡ ከሆነ ፡ የነሱን ፡ አስተያየት ፡ ተከትያለሁ ።

## <u>የቋሚ ፡ መምህራን ፡ ሥራዎች ።</u>

መምህራኑ ፡ ከዘወትር ፡ የማስተማር ፡ ተግባራቸው ፡ በተጨማሪ ፡ በሌሎች ፡ ሥራዎችም ፡ ተሰማርተው ፡ ነበር ።.

<u>ቢልልኝ ፡ ማንደፍሮ</u> ፡— የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀመንበር ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የአካዳሚክ ፡ ኮሚሲዮንና ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ የዕቃ ፡ ግዥ ፡ ክፍል ፡ አባልና ፤ ለዩኒቨርሲቲው ፡ በሕግ ፡ ጠቀስ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ አማካሪ ።

<u>አሌን ፡ ሼዳል</u> ፡— የመንግሥት ፡ ውሎች ፡ (Govt. Contracts) ኮርስ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅተዋል ። በተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ አጠባበቅ ፡ ላሉት ፡ ችግሮች ፡ የንጽጽር ፡ ምርምር ፡ ጥናታቸውን ፡ ቀጥለዋል ። (Doctrate thesis) ለጀርመን ፡ የሕግ ፡ ግምገማ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አበርክተዋል ።

<u>ዳንኤል ፡ ኃይሌ</u> ፡— የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ አዘጋጅ ፡ ለተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ትምህርት ፡ መስጫ ፡ የሚሆኑ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎች ፡ ተቀዳሚ ዝግጅታቸውን ፡ ፈጽመዋል ፤ ስለሕግና ፡ እድገት ፡ የሚያወሳ ፡ አንድ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ ጽፈው ፡ ጨርሰዋል ፤ ይህም ፡ ጽሑፍ ፡ በኡጋንዳ ፡ በሚደረገው ፡ የሕግና ፡ ዕድገት ፡ ጉባዔ ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ የሚታተም ፡ ሲሆን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔትም ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝቶ ፡ በቮልዩም ፡ ፱ ፡ ቁ. ፪ ይታተማል ፤ ተፈጽሞ ፡ ለሚገኘው ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ ማውጫ ፡ ሠንጠረዥ ፡ የበላይ ፡ ተቆጣጣሪ ፤ የዩኒቨርሲቲው ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባዔና ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፡ የምርምርና ፡ የእትም ፡ ጉዳይ ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መኻታ ፡

ቤት ፡ የመተዳደሪያ ፡ ሕግ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ለረዳው ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ ኮሚቴ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሊቀመንበር ፡ በዚህ ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ለትምህርት ፡ ወደ ፡ ሀርቫርድ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ይሄዳል ።

ብሩን ፡ አቶ ፡ ብራይድ ፡—የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ዋና ፡ አዘጋጅና ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የምርምርና ፡ የእትም ፡ ኮሚቴዎች ፡ አባል ፤ ስለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ ለአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫ ፡ አጠናቀዋል ፡ (፲፱፻፷፩-፷፪) ፡ ለንደን ፤ የታንዛንያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለብላውስቴን ፡ (ፍላንዝ) ፤ እንዲሁም ፡ የዓለም ፡ አህጉራት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቶች ፡ ጥናት ፡ አጠናቋል ፡ "ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ በሱዳን" ፡ (the Common Law in the Sudan Verfassung and Reche in Vebers Humburg) የተባለውን ፡ የዛኪ ፡ ሙስጠፋ ፡ መጽሐፍ ፡ ገምግሞ ፡ አሳትሟል ። ለማስተማርያ ፡ የሚሆኑ ፡ ሁለት ፡ ቮልዩሞች ፡ አዘጋጅተዋል ፤ የኢንሹራንስ ፡ ሕግና ፡ እንዲሁም ፡ ለሕግና ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ድንጋጌዎች ፡ (Regulations) ተጨማሪ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅተዋል ። ለጀርመን ፡ ሕግና ፡ እድገት ። (Verfossung and Recht in Vebersee) ፕሮግራም ፡ የመልእክት ፡ አዘጋጅ ፡ በመሆን ፡ አገልግለዋል ። የሲቪል ፡ ሕግ ፡ ሥርዓት ፡ በሚል ፡ ርእስ ፡ በካርቱም ፡ ዩኑቨርሲቲ ፡ ንግግር ፡ ለማድረግ ፡ ተጋብዘው ፡ ነበር ።

ጆን ፡ ኤዲ ፡—ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ በተለያዩ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡ አገልግለዋል ፤ በተጨማሪ ፡ ለረዳት ፡ ዲን ፡ አቶ ፡ ወርቁ ፡ ሥራ ፡ ለማስረከብ ፡ እንደረዳት ፡ ዲን ፡ በመሆንና ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ የዕቅድ ፡ ኮሚቴ ፡ ጸሐፊ ፡ በመሆን ፡ አገልግለዋል ፤ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ በዳረጐት ፡ የሚደረግ ፡ ክፍያ ፡ የሚል ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፱ ፡ ቁ. ፩ ፡ አጠናቀዋል ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፪ ፡ ምርምራቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚሆን ፡ ጽሑፍ ፡ አርቅቀዋል ።

ፋሲል ፡ ናሆም ፡— በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፱ ፡ ቁ. ፪ ፡ ያለውን ፡ የኤርትራ ፡ ሕግ ፡ እንቆቅልሽ ፡ በሚል ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅተዋል ፤ የዩኒቨርሲቲው ፡ የዲሲፕሊንና ፡ የአቤቱታ ፡ ሰሚ ፡ (Grievance) ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀመንበር ፤ የዩኒቨርሲቲው ፡ ፐርሶኔል ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፤ የማታ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ አቀናባባሪ ፤ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ አዘጋጅ ፡ ቦርድ ፡ አባል ።

ፍቅሬ ፡ መርዕድ ፡—የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ማውጫ ፡ (Index) ፕሮጀክት ፡ የበላይ ፡ ተቆጣጣሪ ፤ ስለኢትዮጵያ ፡ የቤተሰብ ፡ ሕግ ፡ (ለዶክትሬት ፡ ጽሑፍ) ምርምራቸውን ፡ ቀጥለዋል ።

ፍሥሐ ፡ ይመር ፡—በዩኒቨርሲቲው ፡ የፋክልቲ ፡ ጉባዔ ፡ አባል ፤ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅ ፤ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ኮሚቴና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፡ ለዓለም ፡ አቀፍ ፡ ድርጅትና ፡ ለዓለም ፡ አቀፍ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሕግ ፡ መማሪያ ፡ የሚያገለግል ፡ ተጨማሪ ፡ ጽሑፎች ፡ አዘጋጅተዋል ።

ግርማ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡— የአስተዳደር ፡ ሕግን ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚጠቅሙ ፡ ዝርዝር ፡ የትምህርቱ ፡ መምሪያ ፡ (Course outline) ፫ ፡ ጥራዝ ፡ የማወዳደሪያ ፡ ጽሑፎችና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በብዛት ፡ የያዘ ፡ ፩ኛ ፡ ጥራዝ ፡ አጠናቀዋል ፤ "ያከራከሩ ፡ ምርጫዎች" ፡ የተባለ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አጠናቀዋል ፤ የአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ ዳጀስት ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፤ እንዲሁም ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡

አስተዳደር ፡ ትእዛዝን ፡ ለማርቀቅ ፡ ረድተዋል ፤ በአስተዳደርና ፡ በምርጫ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ በማማከር ፡ አገልግለዋል ።

ሐጐስ ፡ ኃይሌ ፡—የጀሰፐ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሙት ፡ ኮርት ፡ ውድድር ፡ ተባባሪ ፡ ዲሬክተር ፤ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የአካዳሚክ ፡ ኮሚሲዮንና ፡ የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ ዳይጀስት ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፤ በዲፕሎም ፡ የተመረቁትን ፡ በተለየ ፡ ዝግጅት ፡ ረድተዋል ፤ በወን ጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግና ፡ በታክስ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ምርምራቸውን ፡ ቀጥ ለዋል ።

ጀረሚ ፡ ቲ ፡ ሐሪሰን ፡—የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የምርምር ፡ ጥናትና ፡ የእትም ፡ ፕሮ ግራም ፡ ዲሬክተር ፤ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ አዘጋጆች ፡ ቦርድ ፡ አባል ፤ በሌ ሎች ፡ የአፍሪካ ፡ አገሮች ፡ የሚገኙት ፡ የሕግ ፡ ት/ቤቶች ፡ የሚመጡትን ፡ ገምጋሚ ዎች ፡ (evaluators) ጉብኝት ፡ አስተናባሪ ፤ በናይሮቢ ፡ ኬንያ ፡ በተደረገው ፡ የፍ ትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ /በማክስ ፡ ፕላንክ/ በተዘጋጀው ፡ ስብሰባ ፡ ተካፋይ ፡ ሁነዋል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርንና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግን ፡ የማቀነባበር ፡ ምርምራቸውን ፡ ቀጥለዋል ።

ጆርጅ ፡ ቹቹኖቪች ፡— በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ የሕጎች ፡ ቴዎሪ ፡ መግ ቢያ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በሚወጣ ፡ ድርሰት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ አትመው ፡ አውጥተዋል ። በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል ዩም ፡ ፱ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ የቤተሰብ ፡ ሕግ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ አትመ ዋል ። የኢትዮጵያን ፡ የቤተሰብ ፡ ሕጎች ፡ የሚመለከቱ ፡ ሌሎች ፡ የፈተና ፡ ጥያቄዎች ፡ በመጽሔቱ ፡ ቮልዩም ፡ ፱ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ አውጥተዋል ። በኢትዮጵያ ፡ ስለሃይማ ኖታዊ ፡ ጋብቻ ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ምርምር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ጽሑፎች ፡ አቅርበ ዋል ። በኢትዮጵያ ፡ የውሎች ፡ አሠራርና ፡ ውጤት ፡ ላይ ፡ ምርምራቸውን ፡ ቀጥለዋል ። ለ ፡ (አብሊጌሽን ፡ ቱ) የሚያገለግል ፡ ተጨማሪ ፡ ማስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅተ ዋል ። በሕግ ፡ ት/ቤቱና ፡ በዩኑቨርሲቲው ፡ ለሚገኙት ፡ አያሌ ፡ ኮሚቴዎች ፡ አባል ፤ በኤስ. ዲ. ፒ. ሲ. ሕግ ፡ አርቃቂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ አዘጋጆች ፡ ቦርድ ፡ አባል ፤ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ የንጽጽር ፡ አካዳሚ ፡ አገናኞች ፡ (ራፖርተርስ) ፡ ሊቀ መንበር ፤ ለሚቀጥለው ፡ የአካዳሚው ፡ ስብሰባ ፡ በግል ፡ ሁለት ፡ መግለጫዎችን ፡ በማ ዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። በሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ የጥንት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ጋር ፡ የሥራ ፡ ግንኙነትን ፡ ቀጥለዋል ፡ በት/ቤቱ ፡ የምርምርና ፡ የእትም ፡ ኮሚቴ ፡ የጸ ደቁ ፡ በኢትዮጵያ ፡ (Compensation for damage) ስለጉዳት ፡ ካሣ ፡ ሕግ ፡ የመጀመሪ ያዎቹን ፡ ሁለት ፡ ጽሑፎች ፡ አውጥተዋል ፤ እ. ኤ. አ. በ፲፱፻፸፪ ፡ ዓ. ም. ፡ በተደረ ገው ፡ የምሪቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ (ከዩኒቨርሲቲው ፡ ቻንስለር) ከግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃ. ሥ. እጅ ፡ ከፍተኛ ፡ ሽልማት ፡ እንዲቀበሉ ፡ በሕግ ፡ ት/ቤቱና ፡ በዩኒቨርስቲው ፡ የፋክልቲዎች ፡ ጉባዔ ፡ ተመርጠዋል ።

ፍራንዝ ፡ ላንግ ፡—የውስጥ ፡ ዲስፕሊን ፡ አስተዳደር ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ በሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ለተካሄደው ፡ ሴሚናር ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፤ ላስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ትምህ ርት ፡ የሚሆን ፡ ማስተማሪያ ፡ መጽሐፍ ፡ ማሰናዳታቸውን ፡ ቀጥለዋል ፤ በአፍሪካ ፡ የቀበሌዎች ፡ አስተዳደር ፡ (Local Government) በሚል ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አጠ ናቀዋል ፤ የት/ቤቱ ፡ የቤተ ፡ መጽሐፍት ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፤ የጀርመን ፡ ት/ቤት ፡ ማኅ በር ፡ የሽምግልና ፡ ዳኛ ፡ (Arbiter) ፤ በየካቲት ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሄደዋል ።

ኬንሪች ፡ ሾለር ፡—"የተለየ ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግ" በሚል ፡ ርእስ ፡ መጽሐፍ ፡ አሳት መዋል ። በመጽሐፉም ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ ይገኝበታል ፤ (የታተመው ፡

በጀርመን ፡ አዘጋጅ ፡ ሲ. ኤፍ ፡ ሙለር ፡ ካርልስረሽ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ነው ።) ለሕግ ፡ መንግሥት ፡ ትምህርትና ፡ የሕግ ፡ አጻጻፍ ፡ ዘዴ ፡ የሚለውን ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ እንግሊዘኛ ፡ በመተርጐም ፡ ከመገኘታቸውም ፡ ሌላ ፡ ሕግና ፡ እድገት ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ በካምፓላ ፡ (ዩጋንዳ) በተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ ተካፋይ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ ላስተዳደር ፡ እድገት ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎችን ፡ ማሠልጠን ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ ጽሑፍ ፡ አቅርበዋል ። ጽሑፉም ፡ በስብሰባው ፡ ወቅት ፡ ታድሎአል ፤ በተለይ ፡ በአ. አበባ ፡ የፍ/ቤት ፡ አመሠራረት ፡ ዳኝነትና ፡ እድገት ፡ ላይ ፡ (፲፱፻፳-፲፱፻፴፫) ጥናታቸውን ፡ ቀጥለዋል ፡ "የጀርመን ፡ የመንግሥት ፡ ለውጥ ፡ ፲፰፻፵፰" በሚል ፡ ርዕስ ፡ እንዴት ፡ ሕግ ፡ የሕዝብን ፡ አንድነት ፡ ለመንግሥት ፡ እንደሚረዳ ፡ የሚያስረዳ ፡ ንግግር ፡ ለሕዝብ ፡ አሰምተዋል ።

ሰላሙ ፡ በቀለ ፡—የፋክልቲ ፡ አካዳሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ አባል ፤ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጥናት ፡ ቀጥለዋል ። ለማስተማሪያ ፡ የሚያገለግል ፡ ስለ ፡ ፓርላማ ፡ ፕሮግራም ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ አጠናቀዋል ። የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ የመጻሕፍት ፡ ቤቱን ፡ አርሺቭ ፡ ክፍል ፡ በበላይ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ መርተዋል ።

ሮን ፡ እስክላር ፡—የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ የጄሰፕ ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመለማመጃ ፡ ክርክር ፡ ውድድር ፡ ተባባሪ ፡ ዲሬክተር ። በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ "አውቆ ፡ ስለማጥፋት" የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፯ ፡ ቁ. ፪ ፡ አትመዋል ። በዚህ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ እንዲታተም ፡ የተፈቀደው ፡ ባንድ ፡ በቸልተኛነት ፡ ስለ ፡ መግደል ፡ ፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ አሳባቸውን ፡ ሰንዝረዋል ። "በሕብረተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት" በሚል ፡ ርዕስ ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ አራት ፡ ምዕራፎች ፡ በመጨረስ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። እንዲሁም ፡ "ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ" በሚል ፡ ርዕስ ፡ አንድ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ። የፋክልቲው ፡ የምርምርና ፡ የእትም ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፡ ናቸው ።

ቢ. ጄ. ቴነሪ ፡—በቅርብ ፡ የተጀመረው ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ (Senior Thesis) ፕሮግራም ፡ ተቆጣጣሪ ፡ የፋክልቲው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፡ በናይሮቢ ፡ (ኬንያ) በተደረገው ፡ የንጽጽር ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ስብሰባ ፡ (Comparative Procedural Law Conference) ተካፋይ ፡ ሆነዋል ። የፋክልቲውን ፡ የብሔራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ፕሮግራም ፡ አዘጋጅተዋል ። በኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ሠራተኛና ፡ አሠሪ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉ ፡ ጽሑፎች ፡ ሰብስበዋል ። የዝላይ ፡ ትርኢት ፡ ኮሚቴና ፡ የፈረስ ፡ እሽቅድድም ፡ ክለብ ፡ አባል ፡ ናቸው ። ለሌሎች ፡ ማኅበሮች ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደር ፡ ሕጐች ፡ መሰናዳት ፡ ረድተዋል ። የሕግ ፡ ፋክልቲው ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ የሚያደርገውን ፡ ግንኙነት ፡ መርተዋል ።

ወርቁ ፡ ተፈራ ፡—ረዳት ፡ ዲን ፡ ለአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ "በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አስተዳደር" (Judicial Administration in Ethiopia) በሚል ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አበርክተዋል ። የፋክልቲ ፡ አካዳሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ ጸሐፊ ፡ የዩኒቨርስቲው ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ ጸሐፊ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ። በናይሮቢ ፡ (ኬንያ) ውስጥ ፡ በተደረገው ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ስብሰባ ፡ ተካፋይ ፡ ሆነዋል ። "በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ሞያ ፡ ጥናት" ("Survey of Legal Profession in Ethiopia") የሚል ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ እያዘጋጁ ፡ ናቸው ።

ቴሪ ፡ ጆ. ቨርሄልስት ፡—በአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ ማስፋፋት ፡ ጥናት ፡ ማዕከላዊ ፡ ድርጅት ፡ ተባባሪ ፡ ዲሬክተር ፡ ይህንኑ ፡ ድርጅት ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ የፋክልቲ ፡ አባል ፡ እንዲመራ ፡ ሥራውን ፡ ለማዛወር ፡ በዝግጅት ፡ ላይ ፡ ናቸው ፤ የብላውስታይ

ንና ፡ ፍላንዝ ፡ "የዓለም ፡ አህጉራት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት" በተሰኘው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚታተሙ ፡ የርዋንዳንና ፡ የቡሩንዲን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቶች ፡ አዘጋጅተው ፡ ጨርሰዋል ፤ በተጨማሪም ፡ ስለአፍሪካና ፡ ርዋንዳ ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ጽሑፎችን ፡ አሳትመዋል ።

ዛኪ ፡ ሙስጠፋ ፡—"በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የእስላም ፡ ፍ/ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ ሕግ" በሚል ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ (ቮልዩም ፡ ፱ ፡ ፩) አትመዋል ። በጀርመን ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ በኤይ. ቢ. ዮ. ዛርያ ፡ ሰሜናዊ ፡ ናይጀርያ ፡ ስለሚገኘው ፡ ማእከላዊው ፡ የእስላም ፡ የሕግ ጥናት ፡ ድርጅት ፡ አንድ ፡ መግለጫ ፡ አሳትመዋል ። "ከኮሞን ፡ ሎው ፡ ውስጥ ፡ መምረጥ ፡ "Opting Out of the Common Law" የሚል ፡ የምርምር ፡ ጽሑፋቸውን ፡ የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ተቀብሎታል ፡ ግን ፡ ገና ፡ አልታተመም ። ለብሎስቴን ፡ የዓለም ፡ ሕገ ፡ መንግሥታት ፡ የሱዳንን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ረቂቅ ፡ (Draft) ጨርሰዋል ። እንዲሁም ፡ ለብራስልስ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ "ለሕግ ፡ ታሪክና ፡ አመጣጥ ፡ መግቢያ ፡ የሚረዳ ፡ ጽሑፍ ፡ ምንጭ" "Bibliographical Introduction to Legal History and Ethnology" በሚል ፡ ርዕስ ፡ ረቂቅ ፡ አዘጋጅተዋል ። የፋክልቲው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ። ለእስላም ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ በተጨማሪ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ አሰናድተዋል ። አሁን ፡ ሱዳን ፡ ዲሞክራቲክ ፡ ሪፐብሊክ ፡ መንግሥት ፡ በካቢኔ ፡ ደረጃ ፡ ጠቅላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕግና ፡ የሕግ ፡ መሻሻል ፡ ኮሚሽነር ፡ እንዲሆኑ ፡ ተሾመዋል ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዶሚኒክ ፡ ፕየርስን ፡ ለሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ሲያስተምሩ ፡ በሰጡት ፡ አገልግሎት ፡ ተጠቅመዋል ።

በዚህ ፡ ዓመት ፡ ውላቸውን ፡ ስለፈጸሙ ፡ አሥሩ ፡ የት/ቤታችን ፡ አባል ፡ አስተማሪዎች ፡ አንዳንድ ፡ ቃላት ፡ መጨመር ፡ እፈልጋለሁ ።

ብሩን ፡ ኦቶ ፡ ብራይድ ፡—በጀርመን ፡ አገር ፡ ከነበሩበት ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ የዬል ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ አባል ፡ እንዲሆኑ ፡ ተጨማሪ ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጥቷቸዋል ። ይህ ፡ ለብሩን ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ መጽሐፋቸውን ፡ በጥሞና ፡ ለመጨረስ ፡ ጥሩ ፡ እድል ፡ ነው ። ለሁለት ፡ አድካሚ ፡ ዓመታት ፡ አላንዳች ፡ ጭቅጭቅ ፡ ብዙ ፡ ሥራዎችን ፡ በተለይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ዋና ፡ አዘጋጅ ፡ ሆነው ፡ ከሠሩ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ እድል ፡ ይገባቸዋል ።

አሌን ፡ ሸዳል ፡—ስለ ፡ አካባቢ ፡ ንጽሕና ፡ ለዶክትሬት ፡ ዲግሪ ፡ የሚጽፉትን ፡ ጽሑፍ ፡ ለመሥራት ፡ በበርክሊ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የካሊፎርንያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ነፃ ፡ የትምህርት ፡ ዕድል ፡ ሰጥቷቸዋል ፡ አሌን ፡ ከማንም ፡ ፈረንጣይ ፡ መንግሥት ፡ ከላካቸው ፡ የበጐ ፡ ፈቃድ ፡ አስተማሪዎች ፡ የበለጠ ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ የትምህርት ፡ ሕይወት ፡ ተሳትፈዋል ።

ጆን ፡ ኤዲ ፡—በሰሜን ፡ ካሮላይና ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ይሆናሉ ። ባለፉት ፡ መግለጫዎቼ ፡ እንደ ፡ ረዳት ፡ ዲን ፡ ሆነው ፡ የሠሯቸውን ፡ አስደናቂ ፡ ሥራዎች ፡ በማተኮር ፡ ገልጫለሁ ። ይህ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የት/ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ወደ ፡ ረዳት ፡ ዲኑ ፡ ያላንዳች ፡ እንከን ፡ እንዲተላለፉ ፡ ረድተዋል ። እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ኮሚቴ ፡ ጸሐፊ ፡ ሆነው ፡ የፈጸሟቸው ፡ ተግባሮች ፡ በተለይ ፡ የመጨረሻውን ፡ ረቂቅ ፡ በማዘጋጀት ፡ በማትኮር ፡ (በማድነቅ) ፡ ለመግለጽ ፡

እወዳለሁ ። ከባድ ፡ አስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ቢጫናቸውም ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡
ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አቅርበዋል ። ጆን ፡ ኤዲ ፡ ሥራ ፡ ከጀመሩ ፡
በቅልጥፍና ፡ የሚወዳደራቸው ፡ ማንም ፡ የለም ።

<u>ፍራንዝ ፡ ላንግ</u> ፡—አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ቢሠሩም፡
የዚሁ ፡ ክፍል ፡ መሪ ፡ በኃይል ፡ አመስግነዋቸዋል ። ፍራንዝን ፡ በይበልጥ ፡ የማስታ
ውሳቸው ፡ በተሰጣቸው ፡ ሥራ ፡ ያሳዩት ፡ በነበረው ፡ የመሥራት ፡ ፍላጐትና ፡ ታማኝ
ሪነት ፡ ነው ።

<u>ዛኪ ፡ ሙስጠፋ</u> ፡—ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በሕግ ፡ ፋክልቲያችን ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡
ዓመት ፡ መቆየት ፡ ነበረባቸው ፡ ግን ፡ አገራቸው ፡ ታላቅ ፡ ኃላፊነትና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡
ክብር ፡ ስለጣለችባቸው ፡ ት/ቤቱን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ መሄድ ፡ ግድ ፡ ሆኖባ
ቸዋል ። ዛኪን ፡ አብሪያቸው ፡ በመሥራትና ፡ እንደጓደኛቸው ፡ ለአሥራ ፡ ሁለት ፡
ዓመታት ፡ አውቃቸዋለሁ ። (በመጀመሪያ ፡ ዓመታት ፡ የነበሩን ፡ አንዳንድ ፡ አስደናቂ ፡
የሐሳብ ፡ አለመስማማት ፡ በይበልጥ ፡ እንድንቀራረብ ፡ አድርገውናል) ። ይህንንም ፡
አገጣሚ ፡ ደህና ፡ እንዲሆኑና ፡ ለእርሳቸው ፡ ካለኝ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ትንሹን ፡ ልመግ
ለጽ ፡ እጠቀምበታለሁ ። የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ሊቀና ፡ አስተዳዳሪ ፡ ናቸው ።

<u>ዶሚኒክ ፡ ፐየርስን</u> ፡—በት/ቤታችን ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ አስተምረዋል ። በደ
ንብ ፡ አላውቃቸውም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በከፊሉ ፡ በራሳቸው ፡ ችሎታ ፡ የሚተማ
መኑ ፡ ስለሆነ ፡ የተለየ ፡ ጥንቃቄ ፡ ስላላስፈለጋቸው ፡ ነው ። ይህ ፡ ያልተለመደ ፡ ነው፡
ለዚሁና ፡ ትህትና ፡ ለመላበት ፡ ጠባያቸው ፡ አመስግናቸዋለሁ ።

<u>ሠመረአብ ፡ ሚካኤል</u> ፡—የግል ፡ ጠበቃ ፡ ለመሆን ፡ ት/ቤቱን ፡ ትተዋል ። ት/
ቤቱ ፡ ንቁና ፡ ትልቅ ፡ የመተንተን ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ የሠመረአብ ፡ አእምሮ ፡ አጥ
ቷል ፡ ለዚሁ ፡ አዝናለሁ ፡ ሠመረአብ ፡ ንቁ ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ። በራሳቸው ፡ ሐሳብ ፡
የሚመሩ ፡ ሰው ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ የራሳቸውን ፡ ችግር ፡ በራሳቸው ፡ መንገድ ፡ መወ
ጣት ፡ ግድ ፡ ይሆንባቸዋል ። በብራስለስ ፡ እየተማሩ ፡ ያስጐበኙኝን ፡ ቦታዎች ፡ አልረ
ሳቸውም ።

<u>ሮን ፡ እስክላር</u> ፡—በካናዳ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ የማጊል ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ተባባሪ ፡
ፕሮፌሰር ፡ ይሆናሉ ። ኢትዮጵያን ፡ ከብዙ ፡ ጥሩ ፡ ት/ቤት ፡ ጋር ፡ የሚያገናኝ ፡ አንድ ፡
ሌላ ፡ መስመር ፡ መሥርተዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ሮን ፡ በት/ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ ለአም
ስት ፡ ዓመታት ፡ አስተምረዋል ። ባስተማሩባቸው ፡ ጊዜዎች ፡ በሙሉ ፡ በት/ቤቱ ፡
ውስጥ ፡ አሉ ፡ ከሚባሉት ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ ካላቸው ፡ አስተማ
ሪዎች ፡ አንዱ ፡ ነበሩ ። ሮንን ፡ የሚያውቅ ፡ ሁሉ ፡ የዋህነታቸውን ፡ ያውቃል ። አያሌ፡
የጥናትና ፡ የማስተማር ፡ ጽሑፎች ፡ አስናድተዋል ። የጀመሩትን ፡ የሚፈጽሙ ፡ ሰው ፡
መሆናቸውን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ። ይህንንም ፡ በቅጽበት ፡ ሊገባኝ ፡ የቻለው ፡ በቼስ ፡ ውድ
ድር ፡ ጨዋታችን ፡ ነው ።

<u>ቢል ፡ ቴኒሪ</u> ፡—በአሜሪካን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተመልሰው ፡
በፕሮፌሰርነት ፡ ለማስተማር ፡ ወደአሜሪካ ይመለሳሉ ። ለሦስተኛ ፡ ዓመት ፡ ከኛ ፡
ጋር ፡ እንዲቆዩ ፡ ፈቃድ ፡ በመስጠታቸው ፡ ዕድለኞች ፡ ነን ። ሕግን ፡ በማስተማር ፡
ረገድ ፡ ጥልቅ ፡ ተመክሮ ፡ አላቸው ፡ ይሰጡን ፡ ከነበረው ፡ ምክር ፡ ብዙ ፡ ተጠቅሜ
አለሁ ። በችሎታቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ ካላቸው ፡ አስተማሪዎቻችን ፡ አንዱ ፡
ነበሩ ።

ጆርጅ ፡ ቹቹናቢች ፡—አሁንም ፡ በት/ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያገለግላሉ ። አምና ፡ የተቀበሉትን ፡ ሽልማት ፡ ባምናው ፡ መግለጫዬ ፡ ውስጥ ፡ እንዳልጠቀስ ፡ ዘግይቶ ፡ ስለደረሰኝ ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ መግለጫዬ ፡ ስለሽልማቱ ፡ አንዳንድ ፡ ቃላት ፡ ለመጻፍ ፡ እፈልጋለሁ ። በችሎታቸው ፡ የታወቁና ፡ የተመሠገኑ ፡ የዩኒቨርስቲው ፡ አባሎች ፡ ወደአገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ወይም ፡ አገልግሎታቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ ሲያቋርጡ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የዩኒቨርስቲው ፡ የከፍተኛ ፡ ችሎታ ፡ ሽልማት ፡ ይሰጣቸዋል ። ጆርጅ ፡ ለሃያ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ በሕግ ፡ ትምህርትና ፡ ጥናት ፡ የሰጡት ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ አገልግሎት ፡ ይህን ፡ ሽልማት ፡ ለኔና ፡ ለሕግ ፡ ት/ቤቱ ፡ የጆርጅ ፡ ወደገራቸው ፡ መሄድ ፡ ወይም ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ማቋረጥ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ሆኖ ፡ አልታየንም ። በዚህ ፡ አሳብ ፡ የዩኒቨርስቲው ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ በሙሉ ፡ ድምጽ ፡ ስለተስማማት ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ምረቃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጊዜ ፡ ሽልማቱንና ፡ ሜዳዩን ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ተቀብለዋል ። ፕሮፌሰር ፡ ጆርጅ ፡ በተሰጣቸው ፡ ሽልማት ፡ ሁላችን ፡ ታላቅ ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶናል ።

## የቀድሞ ፡ ተማሪዎችና ፡ የውጭ ፡ ግንኙነቶች ።

የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ትልቅ ፡ ድርጊት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስለተጠቀሰው ፡ የፕሮፌሰር ፡ ቹቹናቢች ፡ ሽልማት ፡ ክብር ፡ ያደረገው ፡ በዓል ፡ ነው ። ኤል. አል. ቢ. ያላቸው ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ተካፍለዋል ። ይህ ፡ አጋጣሚ ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎችንና ፡ አስተማሪዎችን ፡ በጋርዮሽ ፡ የሚጠቅሱ ፡ የሕግ ፡ ጉዳዮችን ፡ ለመነጋገር ፡ አስችሎዋቸዋል ። እንዲሁም ፡ ሥራቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ወደ አገራቸው ፡ ለሚመለሱ ፡ አስተማሪዎቻችንና ፡ ለሚመረቁ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ የማሰና በቱን ፡ ጉዳይ ፡ ለማከናወን ፡ አነስተኛ ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ስብሰባ ፡ አድርገን ፡ ነበር ።

ግን ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ "የሥራ ፡ ቤተሰብ" ስሜት ፡ ለመመሥረት ፡ የወሰድነው ፡ አለጥርጥር ፡ ትልቁ ፡ እርምጃ ፡ በመግቢያዬ ፡ ውስጥ ፡ የገለጥሁትን ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ እርዳታ ፡ ሰጭ ፡ ኮሚቴ ፡ ያከናወነው ፡ ሥራ ፡ ነው ። በተለይም ፡ ጊዜአቸውንና ፡ ችሎታቸውን ፡ አለመቆጠብ ፡ የለገሡልን ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ለማመስገን ፡ እፈልጋለሁ ። እነርሱም ፡ ግርማ ፡ ደሳለኝ ፡ ሕዝቅያስ ፡ አሰፋና ፡ ተስፋዬ ፡ ብርሃኔ ፡ ናቸው ። ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ አለመቋረጥ ፡ ሰርተዋል ። ከቀድሞ ፡ ተማሪአችን ፡ አሁን ፡ በት/ቤታችን ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ ከዳንኤል ፡ ኃይሌ ፡ የበለጠ ፡ የሠራ ፡ የለም ። የኮሚቴው ፡ ጊዜአዊ ፡ ሊቀመንበር ፡ ሆነው ፡ በማገልገል ፡ አያሌ ፡ ጠቃሚ ፡ ሥራዎችን ፡ ሠርተዋል ።

ት/ቤቱንና ፡ የድሮ ፡ ተማሪዎችን ፡ በግልጥ ፡ የሚያስተባብር ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ነገርም ፡ ተፈጽሟል ። እሱም ፡ ውቢትዋና ፡ ቀልጣፋዋ ፡ የዲኑ ፡ ጸሐፊ ፡ መንበረ ፡ ዜና ፡ የቀድሞ ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ መኰንን ፡ ደምሴን ፡ ማግባትዋ ፡ ነው ። ደስታ ፡ የሞላበት ፡ ጋብቻ ፡ እንዲሆንላቸውና ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ አብረው ፡ እንዲኖሩ ፡ እመኝላቸዋለሁ ።

ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ጆን ፡ ኤዲና ፡ ቢል ፡ ቴነሪ ፡ ፋክልቲያችንን ፡ በመወከል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ (የሕግ ፡ መጻሕፍት) የሚሻሻሉበትን ፡ መንገድ ፡ መነጋገር ፡ ጀምረው ፡ ነበር ። የሕጉን ፡ የመሻሻል ፡ ጉዳይ ፡ በአንዳንድ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ቴክኒክ ፡ ማሻሻያዎች ፡ (Technical Amendments) ይወሰን ፡ ወይስ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡

ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ የሚጨበጥ ፡ ለውጥ ፡ ይደረግ ፡ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ እንዲወስን ፡ ትተዋል ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ሚኒስቴሩ ፡ የክፍሎቹን ፡ አስተዳደር ፡ እያረቀቀ ፡ ነው ። ይህ ፡ አሳብ ፡ (ፕሮጀክት) እስከአሁን ፡ በቆይታ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። እንዲሁም ፡ በብዙ ፡ ጉዳዮች ፡ ከሚኒስትሩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የነበራቸው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቴነሪ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አስተማሪዎች ፡ አንድ ፡ ፕሮጂ ፡ ጀምረው ፡ ለወደፊቱ ፡ ሊፈጽሙዋቸው ፡ ለሚፈልጉ ፡ የአገልግሎት ፡ ፕሮጀዎች ፡ ገና ፡ የራሳቸውን ፡ አሳብ ፡ (ውጥኖች) በመመሥረት ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስተማሪዎች ፡ ላይ ፡ መተው፡ የግብዝ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ አሳባቸውን ፡ ገልጠዋል ።

የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሻለቃ ፡ ታደሰ ፡ አብዲን ፡ በእቅድ ፡ ሥራ ፡ ኮሚቴያችን ፡ ፕሮግራም ፡ እንዲሠሩ ፡ በመፍቀዱ ፡ ብዙ ፡ ጠቅሞናል ። ሻለቃውም ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገሮች ፡ አበርክተዋል ።

## ምርምርና ፡ እትሞች ።

አስቀድሜ ፡ እንደጠቀስኩት ፡ የዓመቱ ፡ ትልቁ ፡ ክንውን ፡ የተጠቃለሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዘኛ ፡ ተጽፎ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ መበርከቱ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዳቪድ ፡ ስለ ፡ ውል ፡ ሕጎች ፡ አርእስት ፡ ፲፪ ፡ የጻፉትን ፡ ኪንድረደ ፡ ወደ ፡ እንግሊዘኛ ፡ የተረጐሙትን ፡ ጽሑፍ ፡ አሳትመናል ። በአያሌ ፡ የፋክልቲአችን ፡ ስብሰባዎች ፡ ለሚመጡት ፡ አሥር ፡ ዓመታት ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ ብዙ ፡ የመግለጫ ፡ ጽሑፎች ፡ እንደሚያስፈልጉ ፡ ተስማምተናል ። ሰፊ ፡ የሆነ ፡ አጠቃላይ ፡ የሕግ ፡ መግለጫ ፡ መጻፍ ፡ ተሰብስበው ፡ የተዘጋጀ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችና ፡ አጫጭር ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎችን ፡ ከማዘጋጀት ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳል ፡ ግን ፡ ፋክልቲው ፡ አሁን ፡ በጅ ፡ የሚገኙትን ፡ ለማስተማርያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ስብስብ፡ ጽሑፎች ፡ ለማሻሻልና ፡ ለማብዛት ፡ ለሕግ ፡ ሥራ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎች ፡ ለማውጣት ፡ ከሚደረገው ፡ ተግባር ፡ አጣምሮ ፡ ለማናቸውም ፡ በመጽሐፍ፡ የተጠቃለለ ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ለሚከተሉ ፡ (Code system) ጠቃሚና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ የሕግ ፡ መግለጫዎች ፡ ለማዘጋጀት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ያስፈልጋል ። ፕሮፌሰር ፡ ቹቹኖቪች ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ (Compensation for Damages) የሚለውን፡ ጽሑፋቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ መሆናቸውን ፡ ስገልጽላችሁ ፡ ደስ ፡ እያለኝ ፡ ነው ። የዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ የመጀመሪያ ፡ ዝግጅታቸው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ፡ ውጤት ፡ አስገኝቷል ።

እንዲሁም ፡ የሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ሕጎች ፡ በእውን ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠሩ ፡ ለመረዳት ፡ ለሚደረጉት ፡ ጥናቶች ፡ ያበረታታል ። ለዚሁም ፡ በሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ውስጥ ፡ በኖርዝ ፡ ዌስተርን፡ ዩኒቨርሲቲና ፡ በቀ. ኃ/ሥ. ዩኒቨርሲቲ፡ በተደረጉት ፡ የሁለት ፡ የጥናት ፡ ፕሮጀዎች ፡ ውጤት ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ሆበን ፡ የጻፉት ፡ አማራዊ ፡ የመሬት ፡ አያያዝ ፡ ሁኔታ ፡ (Land Tenure Among the Amhara of Ethiopia) የሚል ፡ መጽሐፍ ፡ በሺካጐ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሬስ ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል ። ቢሆንም ፡ ጥናታቸውን ፡ በሚከታተሉበት ፡ ጊዜ ፡ በሰጠናቸው ፡ እርዳታ ፡ መሠረት ፡ ተባባሪ ፡ ምስጋና ፡ (ጥቅም) ተሰጥቶናል ። በኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ አያያዝ ፡ ሁኔታ ፡ በሚል ፡ ርእስ ፡ ከተጻፈው ፡ ተከታታይ ፡ እትሞቻችን ፡ አራተኛው ፡ ቮልዩም ፡ ነው ።

ጉዳዩን ፡ ከሚመለከታቸው ፡ ባለሥልጣን ፡ ከተመካከርን ፡ በኋላ ፡ በትምህርቱ ፡ ዓመት፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ፒተር ፡ ዊንሺፕ ፡ ያዘጋጁትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳቦች ፡ (Background materials on the commercial Code)

የሚለው ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲታተም ፡ ተልኳል ። ፕሮፌሰር ፡ ጀኮሚ ፡ ሚሌት ፡ ያዘጋጁት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፈጸመቻቸው ፡ (ያደረገቻቸው) ፡ ውሎችና ፡ ሌላ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ስምምነቶች ፡ የዝርዝር ፡ ረቂቅ ፡ (Draft List of Treaties of other International agreements of Ethiopia, 1889 - 1971) የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከሚያሳትማቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ያንኑ ፡ መልክ(ፎርም) ፡ ይዞ ፡ ለመስከረም ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ይታተማል ። የኢትዮጵያን ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ስምምነቶችን ፡ ባንድነት ፡ ለማጠቃለል ፡ የመጀመሪያ ፡ ጥረት ፡ ነው ። የፖልና ፡ ክላፋም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ዕድገት ፡ ያንደኛው ፡ ቮልዩም ፡ ሁለተኛ ፡ እትም ፡ ታትሞ ፡ አልቋል ።

በዚህ ፡ ዓመት ፡ በብዙ ፡ የት/ቤቱ ፡ ፕሮጀዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርምጃ ፡ ተወስዷል ። የኢትዮጵያ ፡ የተጠቃለሉ ፡ ሕጎች ፡ ማተም ፡ ከማለቁም ፡ በላይ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ የማውጫ ፡ ሠንጠረዥና ፡ (Case Index) ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ማውጫ ፡ ሠንጠረዥ ፡ (Code Index) ሥራ ፡ በመግቢያዬ ፡ ላይ ፡ እንደጠቀስኩት ፡ ተጀምሮ ፡ እየተካሄደ ፡ ነው ። ዳንኤል ፡ ኃይሌ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ ማውጫ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ሥራ ፡ ተቆጣጥረዋል ። ካሁን ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተጀምሮ ፡ ያላለቀውን ፡ ሥራ ፡ እግብ ፡ ላይ ፡ በማድረሳቸው ፡ አመሰግናቸዋለሁ ። በብዙ ፡ ፕሮጀዎች ፡ ውስጥ ፡ ዳንኤል ፡ ጥሩ ፡ አስተዳዳሪ ፡ መሆናቸውን ፡ አስመስክረዋል ። አሁን ፡ አስተማሪዎቻችን ፡ የየዓመቱን ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ የያዙ ፡ በሰላሳ ፡ የተጠረዙ ፡ ቮልዮሞች ፡ እየተጠቀሙ ፡ ናቸው ። ተክለ ፡ ገርዝ ፡ ያዘጋጁትን ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ የማውጫ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ፍቅሬ ፡ መርዕድ ፡ በበላይ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ መርምረዋል ። ተክለ ፡ ገርዝ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የሚስማማ ፡ የቋንቋና ፡ የሕግ ፡ ችሎታ ፡ አጣምረው ፡ የያዙ ፡ ሰው ፡ ናቸው ። በያዙት ፡ ሥራ መልካም ፡ እርምጃ ፡ አድርገዋል ። ወደ ፡ አማርኛ ፡ እንግሊዘኛና ፈረንሣይኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የሚመራ ፡ ሥራ ፡ እንደገና ፡ በመጀመሩ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

ፋክልቲአችን ፡ ከሀገር ፡ ልማት ፡ መካነ ፡ ጥናት ፡ ጋር ፡ (Institute of Deveoplment Research) በቀጥታና ፡ (በቦርዱ ፡ ውስጥ ፡ አገልግያለሁ) በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ (የኢንስቲቲዩት ፡ ዲሬክተር ፡ ዶክተር ፡ አሰፋ ፡ ምሕረቱን ፡ ጋብዘን ፡ ከት/ቤታችን ፡ ጋር ፡ አስ ተዋውቀናቸዋል ።) የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ አድርጓል ። እንዲሁም ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ የፓርላማ ፡ ክርክሮች ፡ የማውጫ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ለማውጣት ፡ ለሚደረገው ፡ ጥረት ፡ ይህ ፡ ኢንስቲቲዩት ፡ እንዲያስተባብር ፡ አሳብ ፡ አቅርበናል ። ይህ ፡ ፕሮጀ ፡ መጀመሪያ ፡ እኛ ፡ እንድንሠራው ፡ ተጠይቀን ፡ ነበር ። ብቻችን ፡ ልንሠራው ፡ እንደማንችል ፡ ባስታወቀን ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ፋክልቲዎች ፡ ከሌሎች ፡ ፋክልቲዎች ፡ በመተጋገዝ ፡ ፋንታ ፡ ብቻቸውን ፡ ለመያዝ ፡ ሲሞክሩ ፡ አይተናል ። በዚሁ ፡ ፕሮጀ ፡ አንዳንድ ፡ እርምጃዎች ፡ ተደርገዋል ። ክርክሮቹ ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ የማይክሮ ፡ ፊልም ፡ ፕሮጀ ፡ ውስጥ ፡ ይገቡ ፡ ይሆናል ።

የዩኒቨርሲቲውን ፡ መተባበር ፡ ለሚጠይቀው ፡ ሌላ ፡ አስደናቂ ፡ ፕሮጀ ፡ ደግሞ ፡ ኤፍ. ኤፍ. ራስል ፡ የጻፉቸው ፡ ጽሑፎች ፡ የመሰብሰብ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። እኝህ ፡ ሰውዬ በፌደራስዮን ፡ ጊዜ ፡ ለኤርትራ ፡ የሕግ ፡ አማካሪና ፡ ጠቅላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ነበሩ ። ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ በአሜሪካ ፡ የታወቁ ፡ የሕግ ፡ አስተማሪም ፡ ነበሩ ። ዕድሜአቸው ፡ ከሰማንያ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ሥራ ፡ ቢያቆሙም ፡ ገና ፡ ደልዳላ ፡ ሰው ፡ ናቸው ። ስለኢትዮጵያ ፡ ያላቸው ፡ ትዝታ ፡ በጣም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ። ካራት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ላገኛቸው ፡ በመቻሌ ፡ በጣም ፡ ዕድለኛ ፡ ነኝ ። በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ሲያገለግሉ ፡ የጻፉዋቸው ፡ አያሌ ፡ ጠቃሚ ፡ ጽሑፎች ፡ አሏቸው ። ከጽሑፎቻቸው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ (አስደናቂ) ሆኖ ፡ የሚታዩኝ ፡ ግን ፡ ምናልባት ፡ በየቀኑ ፡ ይጽፉዋቸው ፡ የነበሩት ፡ የራሳቸውን ፡ አስተያየቶችና ፡ ድርጊቶች ፡ የያዘ ፡ ጆርና

ላቸው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ይህ ፡ ጆርናል ፡ ለአጥኝዎች ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ የሶሻልና ፡ የሕግ ፡ መረጃዎች ፡ የያዘ ፡ ምንጭ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ዓመት ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ እቤታቸው ፡ ድረስ ፡ ሄጄ ፡ ባደርግሁት ፡ ጉብኝትና ፡ በዓለም፡ አቀፍ ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ ድርጅት ፡ ሠራተኛ ፡ በሆኑት ፡ በሚስስ ፡ ውድ ፡ እርዳታ ፡ እነዚሁን ፡ ጽሑፎች ፡ በመሰብሰብና ፡ በማስቀመጥ ፡ ላይ ፡ ነን ። ማዕከላዊው ፡ መጻሕፍት ፡ ቤትና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ኢንስቲትዩት ፡ የዚህን ፡ ፕሮጄ ፡ ማለቅ ፡ ለማየት፡ ጓጉተዋል ።

የሕግ ፡ ጥናት ፡ ፕሮጀዎች ፡ እያደጉ ፡ መሄድ ፡ ቀጥለዋል ። ይህም ፡ የአስተማሪዎች ፡ ድርጊቶች ፡ በሚል ፡ አጭር ፡ መግለጫዬ ፡ ተገልጿል ።

እነኝሁ ፡ ድርጊቶችና ፡ የገንዘብ ፡ አስተዳደራችን ፡ መሻሻሉን ፡ ዘርዝሮ ፡ ለማመልጽ ፡ የቻልኩት ፡ የጥናትና ፡ የእትም ፡ ፕሮግራሞችን ፡ ዲሬክተር ፡ በሆኑት ፡ በፕሮፌሰር ፡ ጀረሚ ፡ ሀሪሰን ፡ ድካም ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ የ፳፩ሺህ ፡ የኢት. ብር፡ ገቢ፡ አድርገናል ። ለሚመጡ ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ እንደዚህ ፡ ከቀጠልን ፡ ዩኒቨርሲቲው፡ ለሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ ማሳተሚያ ፡ የሚሆን ፡ የተረጋገጠ ፡ የገንዘብ ፡ አቋም ፡ እንዲኖር ፡ የወሰነውን ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ ትንሽ ፡ ሊቀረን ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የሕግ ፡ እትሞቻችን ፡ የአገሪቱን ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ ለማነፅ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ መሠረታዊ ፡ መሣሪያዎች ፡ ናቸው ።

ባሙቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ጄሪ ፡ ሀሪሰንን ፡ የታተሙ ፡ ጽሑፎች ፡ የመሸጥ ፡ ሥራ ፡ በደንብ ፡ ያካሄዱ ፡ የነበሩ ፡ የወ/ሮ ፡ እሌኑ ፡ አሳዬ ፡ መሰናበት ፡ ምክንያት ፡ አንዳንድ ፡ ችግሮች ፡ አጋጥሟቸው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በወ/ሮ ፡ እሌኒ ፡ ምትክ ፡ ወ/ት የወይንሸት ፡ ደበበን ፡ በማግኘታችን ፡ ታድለናል ። እንደ ፡ ቀዳሚዋ ፡ ሠራተኛ ፡ የእትም ፡ ረዳት ፡ ሥራ ፡ በደንብ ፡ አካሂደዋል ። እንደዚህ ፡ የመሳሰሉ ፡ አያሌ ፡ ችግሮች አጋጥመውናል ፡ በዝርዝር ፡ ግን ፡ አልገልጻቸውም። እነዚህ ፡ ችግሮች ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ምንም ፡ መፍትሔ ፡ ስላልተገኘላቸው ፡ አሁን ፡ በቀላሉ ፡ የሚገኝ ፡ ድል ፡ ለማግኘት ፡ አልሞከርነም። ጄሪንና ፡ ረዳቶቹን ፡(ቡድኑን) ከልብ ፡ የመነጨ ፡ ምሥጋና ፡ ልንሰጣቸው ፡ ይገባል ።

## የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ።

ዋና ፡ አዘጋጅ ፡ ዶክተር ፡ ብሩን ፡ አቶ ፡ ብራይድ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ አጠቃላይ ፡ መግለጫ ፡ እንደሚያዘጋጁ ፡ እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ ነገር ፡ ነው ። የተቀሩት ፡ ሁሉ ፡ ማለት የመጽሔቱን ፡ ዝግጅት ፡ የሚረዱ ፡ መግለጫውን ፡ ቢያነቡ ፡ ጥሩ ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል ።

ዶክተር፡ ብሩን ፡ አቶ ፡ ብራይድና ፡ የቦርድ ፡ አባሎች ፡ ቮልዩም ፡ ፰ ፡ ቁ. ፪ን ፡ አሳትመዋል ። በተጨማሪም ፡ ቮልዩም ፡ ፱ ፡ ቁ. ፩ን ፡ እና ፡ ቮልዩም ፡ ፱ ፡ ቁ. ፪ን ፡ ለአታሚዎች ፡ ሰጥተዋል ። የቮልዩም ፡ ፰ ፡ ቁ. ፩ ፡ ዝግጅት ፡ የሚበዛው ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ ያካሄዱት ፡ እርሳቸው ፡ ናቸው ። መጽሔቱን ፡ የሚያካሄዱ፡ መምህራን ፡ ስማቸው ፡ በግል ፡ መግለጫ ፡ ክፍል ፡ ተዘርዝሯል ። ተማሪ ፡ አዘጋጆች ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ። አንዳርጋቸው ፡ጥሩነህ ፡ ፍርድ ፡ አዘጋጅ ፤ ኃይሌ ፡ ከበደ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅ፤ ጕሹ ፡ ወልዴ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ አዘጋጅ ፤ ኪን ፡ ጥበቡ ፡ ሳህሉ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ፍቅረ ፡ ሥላሴ ፡ ገብረሚካኤል ፡ ተባባሪ ፡ የመጽሔቱ ፡ አዘጋጇዎች ፡ ነበሩ ።

ካለፈው ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ የፋክልቲው ፡ አባሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ዝግጅት ፡ መሰማራት ፡ እየቀጠለ ፡ መሄዱ ፡ ታይቷል ። ነገሩ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እንዲቀጥል ፡ ተፈልጓል ። አቶ ፡ ፋሲል ፡ ናሆምን ፡ የመረጡት ፡ የፋክልቲው ፡ አባሎች ፡ በሙሉ ፡ ናቸው ። መጽሔቱ ፡ እየተሻሻለ ፡ እንደሚሄድ ፡ ተስፋችን ፡ የተሟላ ፡ ነው ። ይህም ፡ ስንል ፡ አቶ ፡ ፋሲል ፡ ዕውቀት ፡ የያዙ ፡ ጽሑፎችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ እያበረከቱ ፡ ስለቆዩና ፡ እንደ ፡ ፋክልቲው ፡ አባል ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ በሥራው ፡ እንደተካፈሉ ፡ ስለምናስታውስ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ እንደ ፡ ተማሪ ፡ አዘጋጅ ፡ ሆነው ፡ ሠርተዋል ።

በዚህ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ የመሻሻል ፡ የመሸጥና ፡ የማደል ፡ ድርጊቶች ፡ በብዛት ፡ የተመረኮዙት ፡ በምርምርና ፡ በእትሞች ፡ ክፍል ፡ ነበር ። በዚህ ፡ አቅጣጫ ፡ እንዲቀጥልም ፡ ይጠበቃል ። በተጨማሪም ፡ የመጽሔቱ ፡ አዘጋጅዎች ፡ የመጽሔቱ ፡ እትሞች ፡ መጠናቸው ፡ እንዲወሰን ፡ የሚያደርገውን ፡ ትልቅ ፡ ቁርጥ ፡ ሀሳብ ፡ ወስነዋል ። ምክንያቱም ፡ የባጀት ፡ ችግር ፡ እንዳያጋጥማቸው ፡ ነው ። ይህንን ፡ ነገር ፡ በማድረጋቸውም ፡ ችግሩን ፡ አስወግደዋል ።

ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ የተደረገው ፡ እድገት ፡ የፋክልቲው ፡ አባሎች ፡ ለመጽሔቱ ፡ ጽሑፎች ፡ ማቅረብን ፡ ያላቸው ፡ ጉጉት ፡ እየጨመረ ፡ በመሄዱ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ዶክተር ፡ ብሩን ፡ ገልጸዋል ። የጽሑፎች ፡ ብዛት ፡ እየቀጠለ ፡ ሲሄድ ፡ ዓይነታቸውም ፡ እንዳልተጓደለ ፡ ዶክተር ፡ ብሩን ፡ የአዘጋጅ ፡ የቦርድ ፡ አባል ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ በተጨማሪ ፡ ገልጸዋል ።

በዚህ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸሙ ፡ ሁናቴዎች ፡ ለወደፊቱ ፡ ሁለት ፡ ትልልቅ ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳዮች ፡ እንዳሉ ፡ አመልክተዋል ። ፩ኛ በሕግ ፡ ፋክልቲና ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሁለቱ ፡ በተባባሪነት ፡ ፳ ፡ የሚሆኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔቶች ፡ አትመው ፡ አውጥተዋል ። ፪ኛው ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ ለመጽሔቱ ፡ የሚወጣውን ፡ ወጪ ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ እንደምንቋቋመው ፡ ነው ።

በመጀመሪያው ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡ ያለኝ ፡ አስተያየት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ከመጽሔቱ ፡ በፊት ፡ ሌላ ፡ የሕግ ፡ እትም ፡ እንዳልነበረ ፡ እንዲታወስ ፡ ይገባል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የመጽሔቱ ፡ የሕግ ፡ እትም ፡ ሆኖ ፡ የተለየና ፡ አጥጋቢ ፡ ጥቅም ፡ አበርክቷል ። አንዳንድ ፡ ጥሩ ፡ ብዬ ፡ የማስባቸው ፡ ነገሮች ፡ በተሟላ ፡ አኳኋን ፡ አይነገርላቸውም ፡ ለማለት ፡ እችላለሁ ። ቢሆንም ፡ መጽሔቱ ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳልነበረ ፡ ለመሆን ፡ እንደሚችልም ፡ ይገባኛል ። ለአሥር ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሲያነቡ ፡ ቆይተዋል ። ማለት ፡ ጠቃሚ ፡ ምርምርና ፡ ክርክር ፡ ሲያነቡ ፡ ቆይተዋል ። የመጨረሻ ፡ አላማው ፡ ይህ ፡ መሆን ፡ የለበትም ። መጽሔቱ ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጥ ፡ የቻለበት ፡ ምክንያት ፡ አንዱ ፡ አሬሻል ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ይሁን ፡ ተብሎ ፡ የተሰጠውን ፡ ምክር ፡ ባለ ፡ መቀበልና ፡ ቀጥሎም ፡ የጆን ፡ ስቲዋርት ፡ ሚል ፡ ተመሳሳይ ፡ ሐሳብ ፡ (ፊሎዞፊ) ይዘው ፡ በመቅረብ ፡ ሐሳባቸው ፡ ቶሎ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲያገኝ ፡ ከሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ባለመስማማቱ ፡ ነው ። ከሚኒስትሩ ፡ የተደረገው ፡ ግንኙነት ፡ በቀላሉ ፡ አልነበረም ፡ ቢሆንም ፡ ተደርሷል ። ለሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ መሪ ፡ ሐሳቦችን ፡ እንደሚያወጡ ፡ እዚህ ፡ ለሚመደቡ ፡ ግዴታቸው ፡ ነው ። በሚወስዷቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ የተነሳ ፡ ከሚመጡት ፡ አሥር ፡ ዓመታት ፡ ወዲያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ይበልጥ ፡ ጥቅም ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲያበረክት ፡ እንደሚያደርጉ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

የገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡ እስከዚህ ፡ የሚያስቸግር ፡ አይደለም ። ገለጻ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። ቢሆንም ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ለሚመጡት ፡

፫ ፡ ወይም ፡ ፬ ፡ ዓመትታት ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚሰጠን ፡ አረጋግጠውልናል ። ይህም ፡ በውጭ ፡ ስጦታ ፡ እንድንጠቀም ፡ የነበረን ፡ የመጀመሪያ ፡ እቅዳችን ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ የሚሄድ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የገንዘብ ፡ አቋማችን በኃይል ፡ የሚያጽናና ፡ ነው ። መጽሔቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሳይቋረጥ ፡ ይቀጥላል ፡ እስከማለትም ፡ ያደርሳል ።

የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ድርጅት ። የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ ዕድገቶችን ፡ በማነጻጸር ፡ አኳኋን ፡ ማጥናት ፡ ለምሁራን ፡ ፍላጐት ፡ ማርካት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን፡ ለወደፊቱም ፡ ጥቅም ፡ አለው ፡ የሚል ፡ ትልቅ ፡ እምነት ፡ አለው ። የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ ዕድገት ፡ ድርጅት ፡ የተመሰረተበት ፡ አንዱ ፡ ምክንያት ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ዕድገቶች ፡ መነጻጸር፡ የሚለውን ፡ ጥናት ፡ ለመማር ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ከአፍሪካ ፡ ውጭ ፡ ሄደው ፡ ከመማር ፡ ፈንታ ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ እንዲከታተሉ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። በዚህ ፡ እምነት ፡ መሠረት ፡ ፋካልቲው ፡ ከፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ በሚያገኘው ፡ አንዳንድ ፡ እርዳታ ፡ ተመርኩዞ ፡ የአፍሪካን ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ከኮሎምቢያ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሚወስድበትን ፡ መንገድ ፡ ባለፈው ፡ ዓመታት ፡ ሲያሰላስል ፡ ቆይቷል ። በተጨማሪም ፡ በኮሎምቢያ ፡ የሚገኙ ፡ የመጽሔቱ ፡ ኃላፊ ፡ ፋክልቲያችንና ፡ ዩኒቨርስቲው ፡ በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ የመጽሔቱን ፡ ሥራ ፡ መቀበል ፡ የሚገባቸው ፡ መሆናቸውን ፡ አረጋግጠዋል ።

ቢሆንም ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ለማሳተም ፡ ለሚደረገው ፡ ጥረት ፡ የፋክልቲያችን ፡ አባሎች ፡ መስማማት ፡ በእርግጥ ፡ አልታወቀም ፡ ነበር ። ስምምነት ፡ አለመኖሩንም ፡ እትሙ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ አለማቋረጥ ፡ ይቀጥላል ፡ የሚል ፡ እምነት ፡ አልነበረኝም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የተነሳ ፡ ሁለት ፡ ሙሉ ፡ የፋክልቲ ፡ ስብሰባ ፡ አድርገን ፡ ስለዚሁ ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡ ተነጋግረናል ። ከስብሰባ ፡ ሌላም ፡ ግላዊ ፡ የሆነ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ተማክረናል ። በመጨረሻም ፡ ፋክልቲው ፡ በመጽሔቱ ፡ የሚጠፋው ፡ ጥረት ፡ ዋጋ ፡ የሚያስገኝ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ተስማምቷል ። በተጨማሪም ፡ ዶክተር ፡ ቨርኽልስት ፡ የድርጅትና ፡ የዋናው ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ሁለተኛ ፡ ዲሬክተር ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ለሚጠይቀው ፡ የደንበኛ ፡ ሂሣብ ፡ ጉዳይ ፡ ፈጽመዋል ። በየካቲት ፡ ወር ፡ በመጨረሻ ፡ ቀኖች ፡ ወይን ፡ ሃሪንግቶን፡ የተባሉ ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ሕግ ፡ ድርጅት ፡ አባል ፡ የአፍሪካን ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ለመመስረት ፡ እንዲረዱ ፡ ለሁለት ፡ ዓመታት ፡ በድርጅቱ ፡ ወደኛ ፡ ተልከዋል ። እርሳቸውም ፡ በኮሎምቢያ ፡ የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ አዘጋጅ ፡ ነበሩ ። እዚህ ፡ ግን ፡ የሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ጉዳይ ፡ ለማጣራትና ፡ መጽሔቱ ፡ ከተለመዱ ፡ የፋክልቲው ፡ ሥራዎች ፡ አንድ ፡ እንዲሆን ፡ ፋክልቲውን ፡ በሚረዱት ፡ ጊዜ ፡ የፋክልቲው ፡ ድጋፍ፡ ያስፈልጋቸዋል ።

ድርጅቱ ፡ በዶክተር ፡ ቫንደርሊንደን ፡ የተደረሱ ፡ ጽሑፎች ፡ ከማሳተሙም ፡ በላይ ፡ ከ፲፱፻፵፪ ፡ ጀምረው ፡ የወጡትን ፡ የአፍሪካ ፡ ሕጐች ፡ መሰብሰብ ፡ ቀጥሏል ።

የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ በፈስተስ ፡ አኪግቤ ፡ መሪነት ፡ የፋክልቲውን ፡ ምርምር ፡ ለማቃለል ፡ በማለት ፡ የሚደነቁ ፡ መሻሻል ፡ አሳይተዋል ። መጽሐፍት ፡ ቤቱ ፡ ፳፬ሺህ ፡ መጻሕፍት ፡ አሉት ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ፪ሺ፫፻፪ ፡ የታዘዙ ፡ መጻሕፍት ፡ እየተጠባበቀ ፡ ነው ። ፈስተስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ኃላፊ ፡ በሕግና ፡ በቤተመጻሕፍት ፡ ጥናት ፡ (Library Science) የተማረ ፡ ቢሆን ፡ የሚያስገኘው ፡ ጥቅም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለዩኒቨርሲቲ ፡ አሳይተዋል ። እንዲሁም ፡ ፈስተስ ፡ በፋክልቲው ፡ በተፈጸሙ ፡ ውጥኖች ፡ ተሳትፈዋል ። ማለት ፡ በሕግ፡ መጻሕፍት ፡ ሠንጠረዥ፡ እና ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ የሕግ፡ መዝገቦች ፡ ክፍል ፡ በተደረገው ፡ የማሻሻል ፡ ጥረት ፡ ተካ

ፍለዋል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ የጽሑፎቹን ፡ የተሻሻለ ፡ አቀማመጥና ፡ አያያዝ ፡ አስገኝተ ዋል ። ይህንንም ፡ ማንኛው ፡ አንባቢ ፡ አይቶ ፡ ሊያመሰግነው ፡ የሚችል ፡ ነው ።

## ሥርዓተ ፡ ትምህርትና ፡ የትምህርት ፡ ደረጃዎች ።

ስለ ፡ የዓመታዊ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የሥርዓት ፡ ትምህርት ፡ ተግባሮችና ፡ ሌሎችም ፡ ማለት ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ጂሰፕ ፡ የመለማመጃ ፡ ክርክር ፡ ውድድርና ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ በመጨረሻ ፡ የሚያቀርቡት ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ በመግቢያ ፡ ተነግረዋል ። ቢል ፡ ተነሪ ፡ ችሎታ ፡ በተሞላበት ፡ አኳኋን ፡ ተማሪዎች ፡ በመጨረሻ፡ የሚያቀርቡት ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ ጉዳይ ፡ አካሄደዋል ። ከፕሮግራሙ ፡ ተያይዘው ፡ የመጡ ፡ ያልታሰቡ ፡ ችግሮች ፡ በማንኛው ፡ አዲስ ፡ ዕቅድ ፡ ላይ ፡ እንደሚደርሰው ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎች ፡ (Senior paper) የስድስት ፡ ሰዓት ፡ ትምህ ርት ፡ ስላላቸው ፡ አርእስታቸውን ፡ መምረጥ ፡ በጥልቅ ፡ የሚታሰብበት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ነበር ። ቢሆንም ፡ ቢል ፡ እያንዳንዱ ፡ ተማሪ ፡ ጥሩ ፡ ማለት ፡ አከራካሪ ፡ አርእ ስት ፡ እንዲያገኙ ፡ አድርገዋል ። ፋክልቲው ፡ ተማሪዎቹ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የምርምር፡ ጽሑፎቻቸውን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ወስኖ ፡ ነበር ። ተማሪዎቹም ፡ ከአንድ ፡ ተማሪ ፡ በስተ ቀር ፡ ውሳኔውን ፡ ተከትለው ፡ ሠርተዋል ። አንድ ፡ ተማሪ ፡ ደግሞ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ባለመከተሉ ፡ ተቀጥቷል ።

## አስተያየት ።

የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ የሚያቀርቡት ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲሻ ሻል ፡ ብዙ ፡ የሚደረጉ ፡ ነገሮች ፡ ይቀራሉ ። ሆኖም ፡ አሁን ፡ ስለተጠቀሰው ፡ የጽሑ ፎች ፡ ጉዳይ ፡ የተደረገው ፡ መሻሻል ፡ ስሜታችንን ፡ የሚያረካ ፡ ነበር ። ጽሑፎቹ ፡ በመጀመሪያ ፡ ዓመታትም ፡ ቢሆን ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የደረሱ ፡ ነበር ። ከታወቁ ፡ የጎረ ቤት ፡ አገሮች ፡ ከመጡ ፡ የተከበሩ ፡ አካዳሚክ ፡ እንግዶች ፡ በተሰጠን ፡ አስተያየት ፡ ሙገሳ ፡ ደስ ፡ ተሰኝተናል ። ለፋክልቲው ፡ እንግዶች ፡ የተደረገው ፡ ወጪ ፡ በከፊል ፡ ድሮ ፡ ከፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ በተገኘው ፡ ስጦታ ፡ ነው ። የገንዘቡን ፡ አብዛኛውን ፡ ክፍ ል ፡ የተጠቀምኩበት ፡ ለሩቅ ፡ አገሮች ፡ እንግዶች ፡ ሳይሆን ፡ ለጎረቤት ፡ አገሮች ፡ እን ግዶች ፡ ነው ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንግዶች ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ሲሸጋገሩ ፡ ስለምንጠራቸው፡ በትንሽ ፡ ወጪ ፡ ጠቃሚ ፡ ምክራቸውን ፡ ለመስማት ፡ ችለናል ።

## የይፋ ፡ እንግዶቻችን ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ፤

### ኬንያ ፤

ዲን ፡ ሳምሙኖሩ ፡ እሳቸውም ፡ ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ የሆነ ፡ ንግግር ፡ ሰጥተዋል ።

ሚስተር ፡ ጆርጅ ፡ ሩክዋሮ ፡ ሚስተር ፡ ሬዲ ፡ ሆድጊን ፡ እን ፡ ሚስተር ፡ ኡክ ፡ (ከለንደን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ በእረፍት ፡ ላይ ፡ ነበሩ) ።

### ሱዳን ፤

ዲን ፡ ሰዒድ ፡ መሐመድ ፡ አህመድ ፡ ኤል ፡ ማህዲ ፡ ስለአገራቸው ፡ ሕግ ፡ ዕድገ ቶች ፡ ለሕዝብ ፡ ክፍት ፡ የሆነ ፡ ንግግርም ፡ ሰጥተዋል ፤ ዶክተር ፡ መሐመድ ፡ ኤል ፋቲህ ፡ መሐመድ ፡ እና ፡ ዶክተር ፡ መሐመድ ፡ አብራሂም ፡ አል ፡ ጣህር ።

ታንዛኒያ ፡

ፕሮፌሰር ፡ ፒ. ኤል ፡ ዮ ፡ ክሮስ ፡ ዲን ፡ ሚስተር ፡ ጆ ፡ ካኒዋኒ ፡ እና ፡ ሚስተር ፡ ቱን ፡ ጐሩ ፡ ሀውራካ ።

ኡጋንዳ ፤

ጊዜያዊ ፡ ዲን ፡ ጆሰፍ ፡ ካኩዛ ፡ ሚስተር ፡ ፍሬድ ፡ ሲምፐብዋ ፡ እና ፡ ሚስተር ፡ ፍራንሲስ ፡ ሰሳኮንዲ ፡ በኡጋንዳ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የሕግና ፡ ዕድገት ፡ ድርጅት ፡ ዲረክተር ።

ዛምቢያ ፤

ፕሮፌሰር ፡ ቤን ፡ ንዋብዌዜ ፡ ዲን ፤ ሚስተር ፡ ሙና ፡ እንዱሎ ፡ የኔ ፡ የድሮ ፡ ተማሪ የነበረውና ፡ እንደ ፡ ጓደኛ ፡ የመጣ ።

ከእንግዶች ፡ ጋር ፡ ስለተማሪዎች ፡ አጻጻፍ ፡ ጉዳይ ፡ በሰፊ ፡ ተነጋግረናል ፤ በተጨማሪም ፡ ሊታወሱ ፡ የሚገባቸው ፡ ስለ ፡ አካዳሚክ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ ተነጋግረናል ፤ አንድ ፡ ነገርም ፡ በጥብቅ ፡ ተገንዝበናል ። እሱም ፡ ከእንግዶቻችን ፡ በብዛት ፡ የኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የአካዳሚክ ፡ ነጥብ ፡ አሰጣጥ ፡ ዘዴ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ የተለመዱ ፡ ነገሮች ፡ መቃወማቸው ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ የነጥብ ፡ አሰጣጥ ፡ ዘዴ ፡ ማለት ፡ ኤ.ቢ. ሲ. ዲ. ኤፍ ፡ አስደሳች ፡ ወይም ፡ አጥጋቢ ፡ ዘዴ ፡ አይደለም ፡ ምክንያቱም ፡ በችሎታቸው ፡ ለተለያዩ ፡ ተማሪዎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ፡ ስለሚያስከትል ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ተናግረዋል ። ሲ. የተባለ ፡ ነጥብ(የአንድ ፡ ተማሪ ፡ ማለፉን ፡ የሚያመለክት) ፡ የሚይዘው ፡ የነጥብ ፡ ርዝመት ፡ ረጂም ፡ መሆኑና ፡ የተማሪዎችን ፡ ችሎታ ፡ ለይቶ ፡ የማያሳይ ፡ መሆኑን ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ጠቅሰዋል ። ሁለተኛ ፡ የዩንቨርሲቲው ፡ የአካዳሚክ ፡ ማዕረግ ፡ (ከፍ ፡ ያለ ፡ ማዓረግና ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማዕረግ) አሰጣጥ ፡ ዘዴ ፡ ማለት ፡ ማዕረጉ ፡ በአምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በተደረገው ፡ የተማሪው ፡ ክንውን ፡ ስለሚመሠርተው ፡ በኃይል ፡ ተቃውመውታል ። ምክንያቱም ፡ ያልተቋረጠ ፡ የተማሪን ፡ መከታተል ፡ ጠልተነው ፡ ሳይሆን ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ዘዴ ፡ ተማሪው ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ በኖረበት ፡ ዓመታት ፡ የሚያሳየውን ፡ እድገትና ፡ በመጨረሻም ፡ ልዩ ፡ ችሎታ ፡ አሳይቶ ፡ የሚጨርስ ፡ ተማሪ ፡ ትንሽ ፡ ዋጋ ፡ በመስጠቱ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ አመልክተዋል ። ይልቅ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሶስት ፡ ዓመታት ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃዎች ፡ የሚጠይቁ ፡ አጠቃላይ ፡ የትምህርት ፡ ጥናቶች ፡ የሚሰጡ ፡ ሆነው ፡ የማዕረጉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻ ፡ ያሉት ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሶስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በተመረጠው ፡ የጥናት ፡ ክፍል ፡ በሚሠሩ ፡ ሥራዎች ፡ እንዲመሠረት ፡ ይገባል ፡ ሲሉ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ሰጥተዋል ።

እንግዶቻችን ፡ ያቀረቧቸውን ፡ ሐሳቦች ፡ የጻፍኩት ፡ ልክ ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ ሳይሆን ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሚያነቃቁና ፡ የሚያሳስቡ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ሌሎች ፡ አቋማችንን ፡ ሲመለከቱ ፡ እንዲታሰብበት ፡ ከሚያደርጉ ፡ ነገሮች ፡ ምሳሌ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

እንደገና ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዩኒቨርሲቲዎች ፡ በውጭ ፡ ፈታኝነት ፡ መልክ ፡ በጥሪ ፡ ሄጃለሁ ። ከ፳፱ ፡ በላይ ፡ የፈተና ፡ ጽሑፎችን ፡ ፰ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶችን ፡ የያዙ ፡ አርሚያለሁ ። በተጨማሪም ፡ ጥቂት ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎችን ፡ የጥናትና ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎችና ፡ ሁለት ፡ የኤል. ኤል. ኤም.

ጽሑፎችንም ፡ አርሚያለሁ ። ጉብኝቱ ፡ የሌሎች ፡ ፋክልቲዎችን ፡ ሥራ ፡ አይቶ ፡ ለመ ፍረድ ፡ ስላስቻለኝ ፡ ትልቅ ፡ ዕድል ፡ ነበረ ፡ እላለሁ ። ፋክልቲዎቹም ፡ ከፍተኛ ፡ የት ምህርት ፡ ደረጃዎች ፡ ይዘዋል ፡ ብዬም ፡ እምናለሁ ።

## ጂሰፕ ፡ የመለማመጃ ፡ ክርክር ፡ ውድድር ።

የፕሮግራሙ ፡ ተባባሪ ፡ ዲረክተሮች ፡ ሮን ፡ እስክላርና ፡ ሐጐስ ፡ ኃይሌ ፡ ነበሩ ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በፕሮግራሙ ፡ ጉዳይ ፡ መሳተፍ ፡ ለሮን ፡ ሶስተኛው ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ለሐ ጐስ ፡ ግን ፡ ሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በመጀመሪያው ፡ ግን ፡ ሐጐስ ፡ በተወዳዳሪነት ፡ መልክ ፡ ነበር ። በመግቢያው ፡ እንደተገለጸው ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ አስገኝቷል ። አንደ ኛው ፡ ጥብቅ ፡ ምርምር ፡ ስለሚጠይቅ ፡ ሁለተኛ ፡ ሐሳቦች ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ቀርበው እንዲፈተኑ ፡ በማስቻሉ ፡ ነው ። ቡድናችን ፡ ከሌሎች ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሲወዳደር ከፍተኛ ፡ ችሎታ ፡ አሳይቷል ። የሚቀጥሉ ፡ ዝርዝሮች ፡ በውድድሩ ፡ የተገኙ ፡ አንዳ ንድ ፡ ውጤቶችን ፡ ያሳያሉ ። የተማሪዎችን ፡ የማሳጠር ፡ ጽሑፍ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ውድድር ፡ አሸናፊ ፡ ከሆነው ፡ የእንግሊዝ ፡ ቡድን ፡ ጽሑፍ ፡ የበለጠ ፡ መሆኑን ፡ በመ ጨረሻ ፡ የደረጃ ፡ ውጤት ፡ ፍርድ ፡ ታይቷል ። ከብርሃኔ ፡ ጊላ ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ውድ ድር ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ የንግግር ፡ ስጦታ ፡ ላሳየው ፡ ተናጋሪ ፡ ጉዳይ ፡ የበለጠ ፡ ምርጫ ፡ ያገ ኘችው ፡ አንድ ፡ ከሕንድ ፡ አገር ፡ የመጣችው ፡ ሴት ፡ ተማሪ ፡ ብቻ ፡ ነበረች ። ሴትየዋ ፡ ሁለት ፡ ሰው ፡ ከያዘው ፡ ቡድን ፡ ቀሪዋእርሷ ፡ ብቻ ፡ ስለነበረች ፡ እንድትከራከር ፡ በመ ጨረሻ ፡ በርህራኄ ፡ መልክ ፡ ተፈቅዶላታል ።

## ለማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ።

ፋክልቲው ፡ ሥራውን ፡ ሲጀምር ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ለወጡት ፡ ሕጎች ፡ ለማጥናት ፡ የሚጠቅሙ ፡ ጽሑፎች ፡ ባስቸኳይ ፡ እንዲዘጋጁ ፡ ተፈልገው ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ ከፍጻሜ፡ ማድረሱ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ነበር ። መጀመሪያ ፡ አስተማሪዎች ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ አነጻጽረው ፡ የሚያሳዩ ፡ ጽሑፎችን ፡ እየተከታተሉ ፡ ነበር ፡ የሚያስተምሩት ፡ ምክንያቱም ፡ ጠቃሚዎች ፡ ስለሆኑ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ለምሳሌ ፡ ፍርዶችና ፡ የአስተዳደር ፡ መግለጫዎች ፡ ለመሰብሰብ ፡ ስለሚያግዙ ፡ ነው ። የኢትዮ ጵያን፡ ጽሑፎች ፡ በጥናት ፡ ለመጨመር ፡ የተደረገው ፡ ጥረት ፡ ድል ፡ ተጐናጽፏል ። እየቀጠለም ፡ ይሄዳል ።

ቢሆንም ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ታትመው ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ፣ አንድ ፡ ጉድለት ፡ ተገንዝቤአለሁ ። እሱም ፡ የስተንሲሎቹና ፡ የባሰም ፡ የመጀመሪያ ፡ ጽሑፎች፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ ስላልተያዙ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እያገለገሉ ፡ ሲሄዱ ፡ ስለሚ ጠፉ ፡ ነው ። ባልታወቀ ፡ አደጋም ፡ ወዲያው ፡ ሊጠፉ ፡ ይችላሉ ።

ሌሎች ፡ የዩኑቨርሲቲ ፡ ፋክልቲዎች ፡ በሚሚዮግራፍ ፡ መልክ ፡ በሚታተሙ ፡ የማ ስተማሪያ ፡ ጽሑፎች ፡ የሚጠቀሙ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ አጋጥሟቸዋል ። የጽሑ ፎችን ፡ መጥፋት ፡ የሚከላከሉ ፡ ብዙ ፡ ዘዴዎች ፡ ለመፍጠር ፡ ሲቻል ፡ አልተደረገም ። ችግሩ ፡ ከዘዴዎቹ ፡ አንዱን ፡ መርጦ ፡ ወደ ፡ ማሠሪያ ፡ ፕሮግራም ፡ መለወጥ ፡ ነው ። ባለፉት ፡ አራት ፡ ዓመታት ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ፕሮግራም ፡ እንዲከፍቱ ፡ ችሎታ ፡ ያላ ቸውን ፡ ካስተማሪዎች ፡ ብዙዎች ፡ መርጠው ፡ ነበር ። ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ስለሚጠ ይቅና ፡ አስተማሪዎች ፡ ጊዜያቸውን ፡ በሙሉ ፡ ለሱ ፡ ብቻ ፡ ለማጥፋት፡ ስለማይችሉ ፡ ነገሩ ፡ ውድቅ ፡ ሆኗል ።

የኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ አገልግሎት ፡ ለመፈጸም ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ለተመለሱት ፡ ለአሌክሳንድራ ፡ ሐማዊ ፡ ከስጠኋቸው ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱ ፡ ፕሮግራሙን ፡ ከፍጻሜ ፡ እንዲያደርሱ ፡ ነበር ። ዕቅዱም ፡ ትዕግሥትን ፡ የቋንቋ ፡ ችሎታን ፡ ማለት ፡ እንግሊዘኛ ፡ አማርኛ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ የአስተዳደር ፡ ችሎታንና ፡ የሕግ ፡ ትምህርትን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ። አለክሳንድራም ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ያልተጠረዙና ፡ የተጠረዙ ፡ ገጾች ፡ ከሦስት ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሕንፃዎች ፡ ማለት ፡ ከየቢሮዎችና ፡ ከየመጋዘኖች ፡ እንዲሁም ፡ ከየድብቅ ፡ ቦታዎች ፡ ሰብስባ ፡ በሚገባ ፡ ባንድነት ፡ አደረገቻቸው ። ባለፉት ፡ አስር ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጽሕፎች ፡ መጥፋታቸው ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ቢሆንም ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ እቅድ ፡ ባይደረግ ፡ ኖሮ ፡ የጽሑፎቹ ፡ መጥፋት ፡ ይበዛ ፡ ነበር ።

፹፪ ፡ ለኤል. ኤል. ቢ. ፕሮግራም ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ አራት ፡ የአማርኛ ፡ ከዲግሪ ፡ በታች ፡ ማለት ፡ ዲፕሎማና ፡ ሰርቲፊኬት ፡ ስለሚያስገኘው ፡ ፕሮግራም ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎችና ፡ የአማርኛ ፡ እስቴንስሎች ፡ ለስምንት ፡ ተጨማሪ ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ አሉ ። የጽሑፎቹ ፡ የመለያ ፡ ቁጥር ፡ ተሰጥቷቸው ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ አርካይቭ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። እንደዚሁም ፡ እስቴንስሎች ፡ የመለያ ፡ ቁጥር ፡ ተሰጥቷቸው ፡ በሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ተይዘዋል ። አወጣጣቸውም ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚወጣው ፡ ነው ።

ለማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ "የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ጓድ" ፡ ባወጣው ፡ መግለጫ ፡ ተዘርዝረዋል ። ቢሆንም ፡ ስለ ፡ ጽሑፎቹ ፡ መሰብሰብ ፡ የተሰጠው ፡ ሥራ ፡ ፍጻሜ ፡ በይበልጥ ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየው ፡ አለክሳንድራ ፡ በሚሚዮግራፍ ፡ መልክ ፡ ያወጡትን ፡ "በሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ አስተማሪዎች ፡ የተዘጋጀው ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ከ፲፱፻፷፫ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፸፪ ።" በሚል ፡ መግለጫ ፡ ነው ። መግለጫው ፡ ፹ ገጾች ፡ አሉት ። ይኸውም ፡ የታተሙትን ፡ ሳይጨምር ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎች ፡ መፍትሔ ፡ ተገኘለት ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ። በዚህ ፡ የተነሳም ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ እንደሌሎቹ ፡ መጻሕፍት ፡ እያያዝ ፡ የማያቋርጥ ፡ አገልግሎት ፡ ይሰጣል ።

## ስለ ፡ ፋክልቲው ፡ የማስተማር ፡ አቋም ፡ አስተያየት ።

በ፲፱፻፸፭ ፡ በሁለተኛው ፡ ሰሚስተር ፡ ተማሪዎች ፡ ስለአስተማሪዎች ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ የሚያሳይ ፡ ምርምር ፡ አድርጌ ፡ ነበር ። ምርምሩ ፡ የሚቀጥሉ ፡ ነገሮችን ፡ አጠቃሏል ። እነሱም ፡ ሊነበቡ ፡ የሚገባቸው ፡ መጻሕፍትን ፡ የሚያሳይ ፡ ዝርዝር ፡ የያንዳንዱ ፡ ጥናት ፡ መግለጫ ፡ እና ፡ ሌሎችንም ፡ ተመሳሳይ ፡ ነገሮች ፡ ይይዛል ። ፳ ፡ ጥያቄዎችን ፡ የሚይዝ ፡ አዲስ ፡ አስተያየት ፡ መስጫ ፡ በዶክተር ፡ ጆንስ ፡ ከዩኒቨርሲቲ ፡ ፈተና ፡ ክፍል ፡ አጋዥነት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ነበር ። በተጨማሪም ፡ ያገኘነው ፡ ጥቅም ፡ አዲሱ ፡ የአስተያየት ፡ መስጫ ፡ በመኪና ፡ ስለመታረም ፡ ነው ፡ ከዚያም ፡ በኮምፒተር ፡ የያንዳንዱ ፡ ጥያቄ ፡ ውጤት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ በደንብ ፡ ይታያል ።

የዚህ ፡ ዓመት ፡ ውጤቶች ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ነበሩ ። ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያገለገሉ ፡ መምህሮች ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ውጤት ፡ አምጥተዋል ። ይህንንም ፡ ስንል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያገለገለ ፡ መምህር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ያገኛል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ከሁሉም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ደግሞ ፡ ከቀንና ፡ ከማታ ፡ ተማሪዎች ፡ ከተሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ሁለት ፡ አዲስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስተማሪዎች ፡ ውጤታቸው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ መሆኑና ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ከተባሉ ፡ አስተማሪዎች ፡ ጋር ፡ በመመደባቸው

ነው ። የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ እየተሻለ ፡ እንደሚሄድ ፡ ከማም ንበት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ቢሆንም ፡ ስለ ፡ ሁለት ፡ አስተማሪዎች ፡ የተሰጠ ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ ለሚያሳ ስብ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ አንዳንድ ፡ ተማሪዎች ፡ ከአስተማሪዎቹ ፡ ባለመግባባታቸው ፡ ሳይሆን ፡ ተማሪዎቹ ፡ በሙሉ ፡ ስላልተደሰቱ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ውጤቱ፡ ለወደፊት ፡ መሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ የሚያበረታታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተስፋ ፡ የሚ ያስቆርጥ ፡ አይደለም ።

## የሥርዓት ፡ ትምህርት ፡ ጥብቅ ፡ ምርምራ ።

ቢልልኝ ፡ ማንደፍሮ ፡—የፋከልቲው ፡ አባል ፡ የሆኑት ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ነው። ስለ ፡ ሥርዓት ፡ ትምህርት ፡ ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ አሳብ ፡ ስለነበራቸው ፡ የሥርዓት ፡ ትምህርትና ፡ የአካዳሚክ ፡ ደረጃዎች ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ እንዲሆኑ ፡ ጠየቅኋ ቸው። አቶ ፡ ቢልልኝ ፡ ከመረጧቸው ፡ የኮሚቴ ፡ አባሎች ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ እያዳንዳን ዳቸው፡ መግለጫ ፡ የመስጠትን ፡ ሥራ ፡ ተካፍለው ፡ ስለ ፡ ማስተማር ፡ ዘዴ ፡ ስለ ፡ ሥርዓት፡ ትምህርት ፡ እና ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፊሎዞፊ (ፊሎዞፊው ስላ ለፉ ፡ ስለአሁንና ፡ ስለሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።) ስለ ፡ ዲግሪ ፡ በታችና፡ በዲግሪ ፡ ደረጃ ፡ በሚገኘው ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራሞች ፡ ጊዜያዊ ፡ መግለጫ ፡ ጽፈዋል ። ሥርዓተ ፡ ትምህርቱም ፡ የሚይዛቸው ፡ ትምህርቶች ፡ ለሕዝቡ ፡ ምን ፡ ዓይ ነት ፡ ጥቅም ፡ እንደሚያስገኙ ፡ ለማወቅ ፡ እያንዳንዱን ፡ ኮርስ ፡ ምርምራ ፡ ጀምረዋል ።

እንዲህ ፡ በማድረጋቸው ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህራን ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ እን ዲመረምር ፡ አነቃቅተዋል ። ይህም ፡ ለፋካልቲው ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ። የመሪ ፡ ሐሳቦች ፡ የፕሮግራም ፡ መልክ ፡ ማስያዝ ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመትም ፡ የሚ ቀጥል ፡ ሥራ ፡ ነው ።

## የዲፕሎማና ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ፕሮግራም ።

የዲፕሎማና ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ፕሮግራም ፡ በኢትዮጵያ ፡ አስተማሪዎች ፡ ሥር ፡ መሆን፡ እንዳለበት ፡ አስተማሪዎቹ ፡ ማቀዳቸው ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የትምህ ርት ፡ መስጫ ፡ ጽሑፎችና ፡ ትምህርቱ ፡ የሚካሄደው ፡ በአማርኛ ፡ ስለሆነ ፡ ፕሮግ ራሙ ፡ ሊካሄድ ፡ የሚችለው ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለፓርላማ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ፕሮግራም ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ተዘጋጅቷል ። ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ አቶ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ከዶ ክተር ፡ ኑነዝ ፡ (ኒዮርክ ፡ ካለው ፡ ስቴት ፡ ዩኒቨርስቲ) ጋር ፡ ተባብረው ፡ የሰበሰባ ቸው ፡ የትምህርት ፡ መስጫ ፡ ጽሑፎች ፡ በአማርኛ ፡ ስላዘጋጁ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ተመሳሳይ፡ ለዳኞች ፡ ፕሮግራም ፡ ጠቅላላ ፡ አቋሙ ፡ እንዴት ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ የሚያሳይ ፡ ሐተታ ፡ (ሐሳብ) ሮን ስክላር ፡ ጽፈዋል ። እንዲሁም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ሕግ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ መከናወን ፡ እንዳለበት ፡ የሚያስረዳ ፡ ኮርስ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አቅርበዋል ።

ቢሆንም ፡ የሚሠራባቸው ፡ ተከታታይ ፡ ፕሮግራሞችና ፡ ከዲግሪ ፡ በታች ፡ ለሚሰ ጡት ፡ ጥናቶች ፡ የሚያገለግሉ ፡ የትምህርት ፡ ጽሑፎች ፡ ሳይቋረጡ ፡ እየታተሙ ፡ ለማ ውጣት ፡ ከተፈለገ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስተማሪዎች ፡ ፕሮግራሞችና ፡ ጽሑፎች ፡ ከአ ዲሱ ፡ የሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ መሪ ፡ ሐሳቦች ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ እንደሚይዙ ፡ አድር ገው ፡ ትልቅ ፡ ጥረት ፡ ካደረጉ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በፋከልቲው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ፡

መምህራን ፡ አብዛኞቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በመሆናቸው ፡ ይህንን ፡ ዓላማ ፡ በሥራ ፡ ለማ ዋል ፡ የሚቻል ፡ ነው ። ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ መምህራኖች ፡ በተለይም ፡ በዶክተር ፡ ብርሃን ፡ ገብራይ ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ ለወደፊቱ ፡ ሥራውን ፡ ያፋጥናል ። በአማርኛ ፡ የተጻፉ ፡ የትምህርት ፡ ጽሑፎች ፡ ስለተፈለጉ ፡ አራት ፡ የሚ ሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ወጥተዋል ። ድሮ ፡ አንድም ፡ ጽሑፍ ፡ አልነበረም ። በተጨማሪም ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የዲግሪ ፡ በታች ፡ ክፍል ፡ አስተዳደር ፡ ከማታ ፡ ትምህርት ፡ ፋክልቲ ፡ ለማስተባበር ፡ የሚያስችሉን ፡ የመጨረሻ ፡ ዝርዝሮች ፡ ጨርሰን ፡ አብቅተ ናል።

ሁለቱ ፡ የዲፕሎማ ፡ ክፍሎች ፡ ከማታ ፡ ትምህርት ፡ ክፍል ፡ በፋሲል ፡ ናሆም ፡ ተባብረዋል ። የታወቁ ፡ የክፍለ ፡ ጊዜ ፡ መምህራን ፡ አገልግሎት ፡ በማግኘታችንም ፡ በጣም ፡ ዕድለኛ ፡ ነን ። እነርሱም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። አቶ ፡ አበበ ፡ ወርቄ ፡ ሻላቃ አበበ ፡ ጓንጉል ፡ ዶክተር ፡ አሰፋ ፡ ሀብተማርያም ፡ አቶ ፡ ሕዝቅያስ ፡ አሰፋ ፡ ሌፍተና ንት ፡ ኮሎኔል ፡ ለገሠ ፡ ወልደማርያም ፡ ሻላቃ ፡ ታደሰ ፡ አብዲ ፡ ዶክተር ፡ ወርቁ ፡ ፈ ረደ ፡ አቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ኃይለማርያም ፡ እና ፡ አቶ ፡ ዘገየ ፡ አስፋው ።

## የፋክልቲው ፡ ጐብኝዎች ።

አስቀድመው ፡ የተጠቀሱት ፡ በአስተያየት ፡ ከረዱን ፡ እንግዶች ፡ ሌላ ፡ ብዙዎች፡ ሌሎች ፡ በጣም ፡ የታወቁና ፡ ጠቃሚ ፡ ምክር ፡ የሰጡን ፡ ጐብኝዎች ፡ ነበሩን ። እነር ሱም ፡ በዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ እንዳመጣጣቸው ፡ ልክ ፡ ስማቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ተዘ ርዝሯል ። ዴቪድ ፡ ኰኸን ፡ ኒው ፡ ዮርክ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ የግል ፡ ሀብታሞች ፡ ከሆነ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ኩባንያ ፡ የመጡ ፡ የመክሲኮ ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ዶክተር ፡ ሮበርት ፡ ሞሊና ፡ ፓስክዋል ። እሳቸውም ፡ የመክሲኮን ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ የሚመለከት ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ። ፖውል ፡ ብሪትዝኪ ፡ ከማላዊ ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ሚስተር ፡ ፕሮካሺያ ፡ ከባለቤታቸው ፡ ጋር ፡ እርሳቸውም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በፔንሲልቫኒያ ፡ ዩኒ ቨርሰቲ ፡ ከፍ ያለ ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ ጨርሰዋል ፤ ፕሮፌሰር ፡ አር ፡ ስክላር ፡ ከኡክላ ፡ (UCLA) የፖለቲካል ፡ ሳይንስ ፡ ክፍል ፡ ሚስስተሪ ፡ ውድ ፡ ከኢንተርናሽናል ፡ (ዓለም ፡ አቀፍ) ፡ የሕግ ፡ ድርጅት ፡ ጠቃሚ ፡ በሆነ ፡ ጉዳይ ፡ መጥተው ፡ ነበር ፡ እርሳ ቸውም ፡ እንደገና ፡ በዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ጐብኝተውናል ፤ ሲኞር ፡ ማሪዛ ፡ ራን ዛቶ ፡ በአሥመራ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ኃላፊ ፡ እርሳቸውም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ትምህርትን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ተወያይተዋል ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጄ. ሲ. ኤን. ፖውል ፡ የቀድሞው ፡ የፋክልቲው ፡ ዲን ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ በሚመለከት ፡ ልዩ ፡ ዓይ ነት ፡ ጉዳይ ፡ ተጠርተው ፡ ነበር ፡ እርሳቸውም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከየቦታው ፡ እንኳን፡ ደህና ፡ መጡ ፡ የማለት ፡ ግብዣ ፡ ቢበዛባቸው ፡ እኛን ፡ ለመጐብኘት ፡ ጊዜ ፡ በማግኘ ታቸው ፡ ልዩ ፡ ችሎታ ፡ እንዳላቸው ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ፡ ሚስተር ፡ ዴቪድ ፡ አንደርስ ንና ፡ ዶክተር ፡ ዊል ፡ ለሜል ፡ ከምሥራቅ ፡ አፍሪካ ፡ ፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እንደገናም ፡ ዊል ፡ ወካይ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ቱኒዝያ ፡ በሔዱበት ፡ ጊዜ ፡ ከሚስታ ቸው ፡ ጋር ፡ ጐብኝተውናል ፡ ሚስ ፡ ሚልድሬድ ፡ ራስል ፡ በዚሁ ፡ መግለጫ ፡ በምር ምር ፡ ክፍል ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሱት ፡ የሚስተር ፡ ኤፍ. ኤፍ. ራስል ፡ ልጅ ፡ ፕሮፌ ሰር ፡ ኮሰው ፡ ከጆርጅ ፡ ታውን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ እርሳቸውንም ፡ ከመስከረም ፡ ወር ፡ ጀምሮ፡ እንደ ፡ መምህር ፡ ሆነው ፡ እንዲሠሩ ፡ ተቀብለናቸዋል ። ሚስተር ፡ ገርድ ፡ እስፕሪን ፡ ሀም በርግ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ በማክስ ፡ ፕላንክ ፡ የጥናት ፡ ድርጅት ፡ የአፍሪካ ፡ ክፍል ፡ ዲሬ ክተር ፡ እርሳቸውም ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ፋክልቲውን ፡ የረዱ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኛ ፡ ነበሩ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዛኪ ፡ ሱንድስትሮም ፡ ድሮ ፡ በፋክልቲያችን ፡ የነበሩ ፡ በሊስቶ ፡ ጥብቅ ፡ የሆነ፡ የሕግ ፡ አማካሪነት ፡ ሥራ ፡ ለመስራት ፡ በመጨረሻም ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሪቻርድ ፡

ጋርድነር ፡ በኮሎምቢያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሮፌሰር ፡ የአሜሪካን ፡ መንግሥት ፡ የቀድሞ ፡ ከፍተኛ ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ከፋክልቲው ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ኢንተር ናሽናል ፡ ሕግ ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ መልካም፡ የሆነ ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ አድር ገዋል ።

## ወደ ፡ ፊት ፡ ስንመለከት ።

ዲን ፡ ፖልና ፡ ዲን ፡ ጆንስን ፡ በመጨረሻ ፡ መግለጫቸው ፡ ላይ ፡ ፋክልቲው ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚያጋጥመው ፡ ችግርና ፡ እንደዚሁም ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ በዝርዝር ፡ ሰጥተዋል ። ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የዲኖቹን ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫዎች ፡ እየተ ከታተለ ፡ ፋክልቲው ፡ ለተነገሩት ፡ ግዳጆች ፡ በመፈጸም ፡ በኩል ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ያስ ገኘ ፡ መሆኑን ፡ ይገነዘባል ።

ለወደፊቱ ፡ ፋክልቲው ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ይኖረዋል ፡ ይኸውም ፡ ለሱ ፡ የተመደበ በው ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ባጀት ፡ በይበልጥ ፡ ጨምሮ ፡ አስቀድሞ ፡ ከውጭ ፡ በሚያገኘው ፡ እርዳታ ፡ ይካሄድ ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ አጠቃሎ ፡ ይዟል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ መጠነኛና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ድርሻ ፡ ከፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ ስለሚያገኝ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የገንዘብ ፡ ድርሻ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ አስተዳደር ፡ ተቀብሎ ፡ በተገቢ ፡ መንገድ ፡ ያስተ ላልፋል ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ እኛ ፡ ከ ፡ USAID በዕርዳታ ፡ መልክ ፡ አዳዲስ ፡ ዕቃዎችን፡ መቀበል ፡ ጀምረናል ። የኛ ፡ ፋክልቲም ፡ ባለፉት ፡ ሶስት ፡ ዓመታት ፡ ያገኘው ፡ ከነበ ረው ፡ የዕቃዎች ፡ ዋጋ ፡ በሃያ ፡ (፳) ሺ ፡ ብር ፡ ዋጋ ፡ የሚበልጡ ፡ ዕቃዎች ፡ ተቀብ ሏል ። እነዚህን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታዎች ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በጣም ፡ የተሳሰረ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ የተነሳም ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ውስጥ ፡ ከሚገባቸው ፡ በላይ ፡ ጊዜ ፡ ወስደውብኛል ። አዲሱ ፡ ዲን ፡ ባመቱ ፡ መጨ ረሻ ፡ የሚመረጥ ፡ መሆኑ ፡ ስለማይቀር ፡ ስለገንዘብ ፡ እርዳታዎቹ ፡ አስተዳደር ፡ የነበ ረኝን ፡ ኃላፊነት ፡ ወደ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሀሪሰን ፡ ማስተላለፍ ፡ ጀመርኩ ፤ ምክንያቱም ፡ ፕሮፌሰሩ ፡ በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ እዚህ ፡ በመኖራቸው ፡ አዲሱ ፡ ዲን ፡ በቀላል ፡ መን ገድ ፡ ኃላፊነቱን ፡ እንዲረከቡ ፡ ተብሎ ፡ ነው ።

በተጨማሪ ፡ ደግሞ ፡ አቶ ፡ ወርቁ ፡ አዲሱ ፡ ዲን ፡ ስለሆኑ፡ ኃላፊነቱን ፡ በሚረከ ቡበት ፡ ጊዜ ፡ በአካዳሚክ ፡ ነክ ፡ ነገሮች ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ አይኖርም ፡ ምክንያቱም ፡ እርሳቸው ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ምክትል ፡ ዲን ፡ ሆነው ፡ በመሥራታቸው ፡ ደግ ሞም ፡ በፋክልቲው ፡ የሦስት ፡ ዓመታት ፡ ልምድ ፡ ስላላቸው ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ አጠናቀው ፡ ስለሚያውቁ ፡ ነው ።